https://chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፫
አዲስ አበባ ጥቅምት ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No. 3
ADDIS ABABA 2nd November 2018

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፬፻፴፫/፪ሺ፲፩ ዓ.ም

የቡና ግብይት እና ጥራት ቁጥጥር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ገጽ.................................... ፲ሺ፭፻፷፰

## Content

Regulation No. 433/2018

The Coffee Marketing and Quality Control Council of Minister Regulation.………………..Page 10568

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር፬፻፴፫/፪ሺ፲፩

## የቡና ግብይት እና ጥራት ቁጥጥርን ለመደንገግ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮ /፪ሺ፯ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፭ እና በቡና ግብይት እና ጥራት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፶፩/ ፪ሺ፱ አንቀጽ ፳፬ (፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ “የቡና ግብይት እና ጥራት ቁጥጥር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፴፫/፪ሺ፲፩” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ:-

፩/ “አዋጅ” ማለት የቡና ግብይትና ጥራት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፶፩/ ፪ሺ፱ ነው፤

Council of Ministers Regulation No. 433/ 2018

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR COFFEE MARKETING AND QUALITY CONTROL

This Regulation is issued by the council of ministers pursuant to Article 5 the definition of the Power and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 916/2015(as amended) and Article 24 (1) of Coffee Marketing and Quality Control Proclamation No. 1051/2017.

## SECTION ONE

## GENERAL

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as “the Coffee Marketing and Quality Control Regulation No. 433/2018”

### 2. Definitions

In this Regulation, unless the context requires otherwise:

1/ "Proclamation" means coffee Marketing and Quality Control Proclamation No.1051/ 2017;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

https://chilot.me



፪/ “የቡና ክምችት ሚዛን” ማለት ማንኛውም በቡና ማምረት ወይም በንግድ ሥራ የተሠማራ ሰው ያመረተውን ወይም የገዛውን ቡና በማዘጋጀት ለገበያ ያቀረበውን እና በመጋዘን ሊገኝ የሚገባው ቀሪ ክምችት ተሰልቶ የሚገኝ ውጤት ነው፤

፫/ “የቡና ናሙና” ማለት ማንኛውም ቡና በሀገር ውስጥ ግብይት እንዲካሄድበት ወይም ወደ ውጭ ከመላኩ በፊት የቡናውን ዓይነትና የጥራት ደረጃ ለመወሰን የሚወሰድ ወካይ ቡና ነው፤

፬/ "ጥብቅ የቡና መጋዘን” ማለት ባለሥልጣኑ በሚሰጠው ፈቃድ መሠረት የውጭ ቡና ገዢዎች የገዙትን ወጪ ቡና በሀገር ውስጥ ተረክበው ለተወሰነ ጊዜ የሚያቆዩበት ደህንነቱ የተጠበቀ መጋዘን ነው፤

፭/ "የቡና ምርት ዘመን" ማለት የቡና ምርት ከተሰበሰበበት ጊዜ ጀምሮ የአንድ ዓመት ጊዜ ነው፤

፮/ "የቡና ምርት ግብይት ዘመን" ማለት በተለየ ሁኔታ በባለሥልጣኑ ካልተራዘመ በስተቀር የቡና ምርት ከተሰበሰበበት ጊዜ ጀምሮ የአንድ ዓመት የግብይት ጊዜ ነው፤

፯/ "የአምራችና ኢንዱስትሪ ትስስር" ማለት በቡና አምራችና በወጪ ቡና ቆዪ ኢንዱስትሪዎች መካከል በውል የሚፈጸም የቡና ማምረትና ሽያጭ አሠራር ነው፤

፰/ "የቡና ምርት ዱካ" ማለት የቡና ምርት ከተመረተበት ጀምሮ እሴት ሰንሰለቱን ተከትሎ ታሪኩን የሚገልጽ መለያ ሰነድ ነው፤

፱/ "የቡና መሸኛ" ማለት በባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል የተዘጋጀ አስፈላጊው መረጃ የተሞላበት፣ የተፈረመበትና የመንግሥት ማህተም ያረፈበት የይለፍ ሰነድ ነው፤

2/ ‘‘Coffee stock balance’’ means a result obtained by calculating carry over coffee stock available in the warehouse and coffee produced, purchased or processed and supplied to the market by any person who engages in coffee production or marketing;

3/ "Coffee Sample" means representative coffee for determining the type and quality standard of any coffee before domestic marketing or export;

4/ “Bonded Coffee Warehouse” means a secured warehouse, where foreign coffee buyers, hoard with permission of the Authority, a purchased export coffee for limited time;

5/ "Coffee Production Season” means one year period starting from coffee harvesting time;

6/ "Coffee Marketing Period" means one year period of coffee marketing starting from coffee harvesting time, unless extended by the Authority in special condition;

7/ “Coffee grower and Industry linkage” means coffee production and sales process, through contractual agreement between coffee producer and export coffee roaster industries;

8/ “Coffee product Trace” means a document that shows the history of a Coffee product beginning from location of production along the value chain;

9/ "Coffee Delivery Note" means a pass permit issued by the authority or appropriate regional organ with necessary information filled, signed and government seal stamped;

https://chilot.me



፲/ "የአቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ" ማለት አግባብ ያለው የክልል አካል የሚያወጣውን የቴክኒክ መስፈርት አሟልቶ የቀይ እሸት ቡና ተፈልፍሎና ታጥቦ የታጠበ ቡና ከነገለፈቱ የሚዘጋጅበትና የሚከማችበት እንደሁም ጀንፈል ቡና ተቀሽሮ፣ ተለቅሞ ያልታጠበ የአቅርቦት ቡና የሚዘጋጅበትና የሚከማችበት በቡና አመራች አካባቢ የተቋቋመ ኢንዱስትሪ ነው፤

፲፩/ "የወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ" ማለት ባስልጣኑ የሚያወጣውን የቴክኒክ መስፈርት አሟልቶ ከነገለፈቱ ያለውን የታጠበ ቡናን ገለፈቱን በማስወገድ የታጠበ ቡና ተበጥሮና ተለቅሞ ለወጪ ገበያ የሚዘጋጅበትና የሚከማችበት እንዲሁም ያልታጠበ አቅርቦት ቡና ተበጥሮና ተለቅሞ ለወጪ ገበያ የሚዘጋጅበትና የሚከማችበት ኢንዱስትሪ ነው፤

፲፪/ "ለግብይት የሚቀርብ የቡና ቅጠል" ማለት በቡና አምራቾች ተሰብስቦ ለገበያ የሚቀርብ ቡና ለተክሉ ተፈጥሯዊ አግልግሎቱን ያጠናቀቀ የቡና ቅጠል ነው፤

፲፫/ በአዋጁ አንቀጽ (፪) የተመለከተው ትርጓሜ ለዚህ ደንብም ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

፫. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ ደንብ በኢትዮጵያ የቡና ግብይትና ጥራት ቁጥጥር ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሚሳተፍ ማንኛውም ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

10/ "Supply coffee processing and warehousing industry" means industry established fulfilling the technical requirement issued by appropriate regional organ in coffee growing areas, in which red chary coffee is pulped and washed to be processed and stored as washed coffee with parchment and also coffee with pulp is hulled, cleaned and sorted to be processed and stored as unwashed supply coffee;

11/ "Export coffee processing and warehousing industry" means industry established fulfilling the technical requirement issued by the Authority, in which washed coffee with parchment is hulled, cleaned and sorted to be processed and stored as washed export coffee and also unwashed coffee is hulled, cleaned and sorted to be processed and stored as unwashed export coffee;

12/ "Coffee leaf supplied for market" means coffee leaf collected and supplied to the market by coffee producers after completing its natural use for coffee tree;

13/ Definitions provided under Article (2) of the Proclamation shall also be applicable for this Regulation.

3. **<u>Scope of Application</u>**

This Regulation shall apply to any person who directly or indirectly involves in coffee marketing and quality control.

https://chilot.me


## ክፍል ሁለት

## የቡና ግብይት አሠራር

**፬. የቀይ እሸትና የጀንፈል ቡና ግብይት**

ማንኛውም የቀይ እሸት እና የጀንፈል ቡና ግብይት የሚከናወነው:-

፩/ የቡና አምራች አርሶ አደሮች ከግል ቡና አቅራቢዎች ወይም ከመሠረታዊ ህብረት ሥራ ማህበራት ጋር በተፈቀደ የታጠበ እና ያልታጠበ ቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች ተደራሽ ባልሆኑባቸው ወይም በሌሉባቸው አካባቢዎች በሚቋቋሙ በመጀመሪያ ደረጃ ቡና ግብይት ማዕከላት፤

፫/ የቡና ልማትና ግብይት ትስስር በፈጠሩ ቡና አምራች አርሶ አደሮችና አልሚ ባለሃብቶች መካከል በውል ስምምነቱ በተገለጸ ቦታ፤ እና

፬/ የወጪ ቡና ቆዪ ኢንዱስትሪዎች ከቡና አምራች አርሶ አደሮች ጋር በምርትና ግብይት ውል ስምምነቱ በተገለጸው ቦታ ነው፡፡

**፭. የአቅርቦትና ተረፈ ምርት ቡና ግብይት**

፩/ የአቅርቦት ቡና ግብይት በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በሌሎች አማራጭ የቡና ግብይት ሥርዓት ብቻ ይከናወናል፣

፪/ ማንኛውም ተረፈ ምርት ቡና ግብይት የሚካሄደው በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ብቻ ነው፡፡

፫/ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚካሄድ የቡና ግብይት:-

ሀ) ቡና አቅራቢ ወይም ቡና አምራች የአቅርቦት ወይም የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ብቻ በመሸጥ፣

## SECTION TWO

## COFFEE MARKETING PROCESS

**4. Marketing of Red Cherry coffee and Coffee with pulp**

Marketing of red cherry coffee and coffee with pulp shall take place:

1/ At allowed washed and unwashed coffee processing industries, between suppliers or primary co-operatives and coffee growing farmers;

2/ Without prejudice to the provision of sub article (1) of this article, at first level coffee transaction centers where coffee processing industries are inaccessible or nonexistent;

3/ At the place mentioned in the contractual agreement of established out growers scheme, between coffee growing farmers and commercial coffee producers; and

4/ At the place mentioned in the contractual agreement between coffee growing farmers and export coffee roaster industries.

**5. Marketing of Supply Coffee and Coffee By Product**

1/ Supply coffee transaction shall take place only at Ethiopian Commodity Exchange or at another alternative marketing system,

2/ Any coffee by product transaction shall take place only at Ethiopian Commodity Exchange,

3/ In Ethiopia Commodity Exchange:

a) a coffee supplier or coffee grower shall only sell supply coffee or domestic consumption coffee,

https://chilot.me



ለ) ቡና ላኪ ለወጪ ገበያ የሚሆን የአቅርቦት ቡና በመግዛትና ተረፈ ምርት ቡና ብቻ በመሸጥ፣

ሐ) የወጪ ቡና ቆዪ የአቅርቦት ቡና ወይም የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና በመግዛትና ተረፈ ምርት ቡናን ብቻ በመሸጥ፣

መ) የሀገር ውስጥ ቡና ጅምላ ነጋዴ የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ወይም ተረፈ ምርት ቡናን ብቻ በመግዛት፣ እና

ሠ) የሀገር ውስጥ ቡና ቆዪ የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ወይም ተረፈ ምርት ቡናን ብቻ በመግዛት፤

ይከናወናል፡፡

፬/ ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም ከሌሎች የግብይት አማራጮች የተገዛ የአቅርቦት ቡና በድጋሚ በሀገር ውስጥ ሊሸጥ አይችልም፤

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ቡና ላኪ የቡና ላኪነት ሥራውን ያቋረጠ ከሆነ ወይም የውጭ ገበያ ማጣቱን አሳማኝ ማስረጃ ያቀረበ ከሆነ ወይም ከውጪ ገበያ ሽያጭ ተርፎ ሳይላክ የቀረ አነስተኛ መጠን ያለው ቡና መኖሩ ሲረጋገጥ በባለሥልጣኑ ልዩ ፈቃድ ብቻ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በስምምነት በሌላ ቡና ላኪ በውጭ ገበያ ሊሸጥ ይችላል፡፡

፮/ ቡና አምራች አርሶ አደሮች ያመረቱትን የአቅርቦት ወይም ተረፈ ምርት ቡናን አግባብ ባለው የክልል አካል ተረጋግጦ ንግድ ፈቃድ ሳይጠየቁ በሚሰጣቸው ልዩ ፈቃድ ብቻ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ መሸጥ ይችላሉ፡፡

b) a coffee exporter shall only purchase export standard supply coffee and sell coffee by product,

c) an export coffee roaster shall only purchase supply coffee and domestic consumption coffee and sell coffee by product,

d) a coffee wholesaler shall only purchase domestic consumption coffee or coffee by product, and

e) a domestic coffee roaster shall only purchase domestic consumption coffee or coffee by product.

4/ Supply coffee purchased from Ethiopian Commodity Exchange or other alternative market system shall not be re- sold in domestic market.

5/ Without prejudice to the provisions of sub-article (4) of this Article, any coffee exporter who closed his exporting business or provide convincing evidence on lack of export market or have small quantity of export coffee leftover from export, may sell at the Ethiopian Commodity Exchange or at export market through agreement with other coffee exporter, only when it is verified and permitted by the Authority.

6/ Coffee growing farmers may sell supply coffee or coffee by product at Ethiopian Commodity Exchange without trade license, when this is verified and permitted by appropriate regional organ.

https://chilot.me



**፮. <u>አማራጭ የቡና ግብይትና አሠራር</u>**

፩/ ቡና ላኪ ወይም የወጪ ቡና ቆዪ ከቡና አቅራቢ ወይም ከቡና አልሚ ባለሃብት ጋር የቀጥታ የአቅርቦት ቡና ግብይት ትስስር የሚፈጥረው:-

ሀ) በተዋዋይ ወገኖች መካከል ቢያንስ ለሁለት ዓመት የሚቆይ ስልጣን ባለው አካል የተመዘገበ የውል ስምምነት ሲኖር፣

ለ) የተመዘገበው ውል በአስራ አምስት የስራ ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ ቀርቦ የጸደቀና በሦስት የስራ ቀናት ውስጥ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ቀርቦ የተመዘገበ ሲሆን፣

ሐ) በውል ስምምነቱ የርክክብ ቦታው የተገለጸና የርክክብ ጊዜው የምርት ዘመኑ ሳያልፍ ስለመሆኑ በግልጽ የተጠቀሰ ከሆነ፣

መ) የተዋዋይ ወገኖች የግብይት ዋጋ ስምምነቱ በቡና ጥራትና ደረጃ ምደባ ማዕከል የቡናው ጥራት ደረጃ በተሰጠበት ቀን በኢትዮጵያ ምርት ገበያው በሚኖር ተመሳሳይ ዓይነትና ደረጃ ያለው ቡና አማካይ ዋጋ በላይ ከሆነና ጭማሪውም በመቶኛ በውሉ የተገለጸ ከሆነ፣

ሠ) ቡና አቅራቢው ወይም ቡና አልሚ ባለሃብቱ ከሚያዘጋጀው ቡና ከ፸፭ በመቶ (ከሰባ አምስት በመቶ) በላይ ጥራቱ ከደረጃ አንድ እስከ ደረጃ አራት በማድረግ ለማስረከብ በውሉ የተስማማ ከሆነ፣

ረ) ቡና ላኪው ወይም የወጪ ቡና ቆዪ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከተመዘገበው ተመሳሳይ የቡና ዓይነት፣ ደረጃ እና መዳረሻ ገበያ አማካይ ዋጋ በላይ በውጭ ገበያ ለመሸጥ የተስማማ ከሆነ፣

6. **<u>Alternative Coffee Transaction and Process</u>**

1/ Coffee exporter or export coffee roaster may establish supply coffee transaction scheme with coffee supplier or Commercial Coffee producer, if :

a) there is a contractual agreement registered by the authorized organ between contracting parties for a minimum of two years,

b) the Registered contract is approved with in fifteen working days starting from the date of registration by Authority and thereafter registered with in three working days by Ethiopian commodity exchange,

c) the place of delivery is indicated in the contract and it is clearly stated in the contract that the time of delivery should not be after the end of coffee production year,

d) The agreement of the price by Contracting parties' is above the average price of similar coffee type and grade at Ethiopian Commodity Exchange, on the same date the coffee is graded by the coffee quality inspection and grading center and the additional payment is specified in the contract with percentage,

e) The Coffee Supplier or commercial Coffee producer agrees in the contract only to deliver above 75% (seventy five percent) from grade one up to four from all processed coffee,

f) The coffee exporter or export coffee roaster agrees to sell higher than the average price of export coffee market registered by National Bank of Ethiopia of the same type, grade and destination,

ሰ) ሁለቱም ወገኖች በውል አፈጻጸም ላይ አለመግባባት ቢከሰት በድርድር ወይም አግባብ ባለው ፍርድ ቤት ለመዳኘት መስማማታቸው በውሉ የተገለጸ ከሆነ፣ እና

ሸ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሥር ከፊደል ተራ (ሀ እስከ ረ) የተመለከቱ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው የተለየ የገበያ ዕድል ወይም የተሻለ ዋጋ ለማግኘት ከሴት ቡና አምራች፣ ከሴት ቡና ላኪ ወይም ከሴት የውጪ ቡና ቆዪ ጋር በቀጥታ የቡና ግብይት ለመፈጸም በውል የተስማሙ ከሆነ፤

ነው፡፡

፪/ ቱቡና አቅራቢ የወጪ ገበያ ቡናን በቀጥታ ወደ ውጭ ሀገር መላክ የሚችለው:-

ሀ) ከቡና አቅራቢነት በተጨማሪ የቡና አቅራቢ፣ ላኪነት የብቃት ማረጋገጫና የቡና ላኪነት የንግድ ፈቃድ ካለው፤

ለ) በራሱ ኢንዱስትሪ ከሚያዘጋጀው ቡና ከ፸፭ በመቶ (ከሰባ አምስት በመቶ) በላይ የሚሆነው ጥራቱ ከደረጃ አንድ እስከ ደረጃ አራት ከሆነና ዱካውን ጠብቆ ወደ ውጭ ገበያ ለመላክ ከተስማማ፤ እና

ሐ) በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከሚመዘገበው ተመሳሳይ የቡና ዓይነት፣ ደረጃ እና መዳረሻ ገበያ አማካይ ዋጋ በላይ በውጭ ገበያ ለመሸጥ ከተስማማ፣

ነው፡፡

፫/ ቡና አምራች አርሶ አደር በቀጥታ ቡናን ለውጭ ገበያ መላክ የሚችለው:-

ሀ) የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ያለው፣ በቡና የተሸፈነ መሬት መጠንና በየዓመቱ የሚመረተውን የቡና ምርት ግምት ማስረጃ አግባብ ካለው የክልል አካል የሚያቀርብ ከሆነ፣

g) there is an agreement in the contract to resolve disagreement between contracting parties either by negotiation or by court, and

h) Without prejudice to the conditions under sub-article 1(a–f) of this Article, a women coffee growing farmer agrees in contract to transact coffee directly with women coffee exporter or women export coffee roasters to obtain special market opportunity or premium price.

2/ Coffee Supplier may export directly export coffee when he:

a) holds supplier-exporter certificate of competence and coffee export trade license in addition to coffee suppliers;

b) Agrees to export above 75% (seventy five percent) from grade one up to four by maintaining traceability, form coffee processed in his industry; and

c) Agrees to sell higher than the average price of National Bank of Ethiopia export coffee contract registration of the same date, coffee type, grade and destination.

3/ Coffee producing farmer may export coffee directly to foreign market when he:

a) Submits evidence of land holding certificate, amount of coffee plantation land and its estimate of annual coffee production from appropriate regional organ,

https://chilot.me



ለ) የአቅርቦት እና የወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ያለው ወይም የኪራይ ውል ያለው ስለመሆኑ የሚያቀርብ ከሆነ፣

ሐ) በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የቡና አምራች አርሶ አደሮች በተመሳሳይ ጊዜ ካስመዘገቡት ተመሳሳይ የቡና ዓይነት፣ ደረጃ እና መዳረሻ ገበያ ሽያጭ ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ ለመሸጥ ከተስማሙ፣ እና

መ) ከማሳው ያመረተውን ቡና ብቻ ለመላክ ንግድ ፈቃድ ሳያስፈልገው ከባለሥልጣኑ ቡና የመላክ ልዩ ፈቃድ የተሰጠው ከሆነ፤

ነው፡፡

፬/ ቡና አልሚና ላኪ ባለሃብት በቀጥታ ቡናን በውጭ ገበያ መለክ የሚችለው:-

ሀ) የኢንቨስትመንት ፈቃድ፣ የመሬት ኪራይ ውል፣ በቡና የተሸፈነ መሬት መጠንና ዓመታዊ የቡና ምርት ግምት አግባብ ካለው የክልል አካል ማስረጃ ካቀረበ፣

ለ) ከቡና አምራች አርሶ አደሮች ጋር የልማትና ግብይት ትስስር የፈጠረ እና ስለዚህ ሁኔታ አግባብ ካለው የክልል አካል ማስረጃ ካቀረበ፣

ሐ) የአቅርቦት እና የወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ያለው ወይም የኪራይ ውል ያለው ስለመሆኑ የሚያቀርብ ከሆነ፣ እና

መ) ቡና አልሚና ላኪ ባለሃብቶች በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በተመሳሳይ ጊዜ ካስመዘገቡት ተመሳሳይ የቡና ዓይነትና ደረጃ የመዳረሻ ገበያ አማካይ ዋጋ እና በላይ በውጭ ገበያ ለመሸጥ የተስማሙ ከሆነ፤

ነው፡፡

፭/ የወጪ ቡና ቆዪ በአምራችና ኢንዱስትሪ ትስስር ቡና ገዝቶ ወደ ውጭ መላክ የሚችላው:-

b) Submits ownership evidence or lease contract of supply and export coffee processing and warehousing industry,

c) Agrees to sell with similar export price registered by coffee growing farmers at National Bank of Ethiopia of the same time, type, grade and destination, and

d) Holds special coffee export permit from the Authority to export only coffee produced from his own farm without export trade license.

4/ coffee producer and exporter may export coffee directly to foreign market when he:

a) Submits evidence of Investment license, land lease certificate, amount of coffee plantation land and its estimate of annual coffee production from appropriate regional organ,

b) Establishes out grower's scheme with coffee growing farmer and submits evidence about this from appropriate regional organ,

c) Submits ownership evidence or lease contract of supply and export coffee processing and warehousing industry, and

d) Agrees to sell with average and above export price registered in similar time by commercial coffee producers at National Bank of Ethiopia of the same time, type, grade and destination.

5/ Export coffee roaster may export coffee by purchasing coffee through ccontract farming, when he:

https://chilot.me



ሀ) ቀይ እሸት ወይም ጀንፈል ቡና ከአምራች አርሶ አደሮች በአምራችና ኢንዱስትሪ ትስስር ከገዛ፣

ለ) የገዛውን ቡና የጥራት ደረጃና የምርት ዱካ ጠብቆ ቆልቶ ወይም ቆልቶና ፈጭቶ ወደ ውጭ ለመላክ ከተስማማ፣ እና

ሐ) የወጪ ቡና ቆዪዎች በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በተመሳሳይ ጊዜ ካስመዘገቡት የቡና ዓይነትና ደረጃ መዳረሻ ገበያ አማካይ ዋጋ በላይ በውጭ ገበያ ለመሸጥ የተስማሙ ከሆነ፣

ነው፡፡

## ፯. የልዩ ቡና ዝግጅትና ግብይት አሰራር

፩/ የልዩ ቡና ዝግጅትና ግብይት የሚፈጸመው:-

ሀ) ቀይ እሸት ወይም ጀንፈል ቡና ለልዩ ቡና ዝግጅት ግብዓትነት ለመጠቀምም ሆነ ለማዘጋጀት የባለሥልጣኑን የቴክኒክ መስፈርትና የጥራት ደረጃ ያሟላ ከሆነ፣

ለ) ማንኛውም ቡና አቅራቢ ወይም አምራች ያልታጠበ ልዩ ቡና ለማዘጋጀት አግባብ ካለው የክልል አካል የብቃት ማረጋገጫና ፈቃድ ያገኘ ከሆነ፣

ሐ) የልዩ ቡና የግዢ፣ የዝግጅት፣ የክምችትና የሽያጭ መረጃ በተለየ መልኩ ሲይዝና ሊቀርብ የሚችል ከሆነ፣ እና

መ) በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በአማራጭ ግብይት ሲፈጸም ልዩ ቡና ተብሎ ከተመዘገበ፣

ነው፡፡

፪/ ማንኛውም ቡና አቅራቢ ለልዩ ቡና ዝግጅት ከቡና አምራች አርሶ አደሮች ጋር የልዩ ቡና ልማትና ግብይት የትስስር ውል ሲያደርግ:-

a) Purchases red cherry coffee or coffee with pulp from coffee growing farmers through coffee grower and Industry contract linkage,

b) Agrees to export purchased coffee by roasting or roasting and grinding according to the coffee quality standard and insured its traceability and

c) Agrees to sell above average price of export coffee registered by coffee export roasters in similar time at National Bank of Ethiopia of the same coffee type, grade and market destination.

## 7. Specialty coffee preparation and Transaction process

1/ Specialty coffee preparation and transaction shall be executed:

a) When red cherry coffee or coffee with pulp that can be used as input for or processing of specialty coffee fulfills the technical requirements and quality standards issued by the Authority,

b) When any coffee supplier or producer obtains certificate of competence and permission from appropriate regional organ for unwashed specialty coffee preparation,

c) When information on specialty coffee purchase, process, storage and sells managed differently and can be provided, and

d) When it is registered as specialty coffee during transaction at Ethiopian Commodity Exchange or at Alternative marketing system.

2/ When any coffee supplier establishes out grower's scheme agreement with coffee growing farmers for specialty coffee preparation, he shall:

https://chilot.me



ሀ) ለቡና አምራች አርሶ አደሮቹ ምርትና ምርታማነትን የሚያሳድጉና ጥራትን የሚያሻሽሉ የኤክስቴንሽን ድጋፍና ቴክኖሎጂ ለማቅረብ መስማማት፤

ለ) ለቡና አምራች አርሶ አደሮቹ የኤክስቴንሽን ድጋፍ ለመስጠት አግባብ ያለው ባለሙያ በቅጥር ለማሠማራትና የቴክኖሎጂ ድጋፍ ለማድረግ አቅም ያለው ስለመሆኑ አግባብ ካለው የክልል አካል ማስረጃ ማቅረብ፤

ሐ) ከቡና አምራች አርሶ አደሮቹ ከተረከበው ቡና ከ፺ በመቶ (ከዘጠና በመቶ) በላይ በልዩ ቡናነት ለማዘጋጀት መስማማት፣ እና

መ) ለልዩ ቡና ዝግጅት ለሚረከበው ቡና ከአካባቢው ገበያ ዋጋ በላይ ለመክፈል መስማማት፣

አለበት፡፡

**፰. <u>ከውጭ ሀገር ስለሚገባ ጥሬ ቡና</u>**

፩/ ከውጭ ሀገር ቡና ለማስገባት የሚቻለው:-

ሀ) ጥሬ ቡናን ከውጭ ሀገር ማስገባት የሚኖረው ሀገራዊ ፋይዳ በጥናት ሲረጋገጥ፣

ለ) ከውጭ ሀገር ተፈቅዶ የሚገባው ጥሬ ቡና የተመረተበት ሀገር የተገለጸ እና ሀገራዊ የዕጽዋት ጤና ማረጋገጫ መስፈርት ሲያሟላ፣

ሐ) ከውጭ የሚገባው ጥሬ ቡና የተፈቀደለትን የጉዞ መስመር፣ መጋዘንና ኢንዱስትሪ ብቻ የሚጠቀም ከሆነ፣

መ) ከሀገራችን ቡና ጋር በሚታወቅ ምጣኔ ተቀይጦ በተቆላ ወይም ተቆልቶ በተፈጨ ወይም በሌላ መልኩ እሴት ተጨምሮ ሙሉ በሙሉ ወደ ውጭ ገበያ የሚላክ ከሆነ፣

ነው፡፡

፪/ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ከውጭ ለሚገባ ጥሬ ቡና ልዩ የጉምሩክ ማስተናገጃ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

a) Agree to provide extension service and technology to increase productivity and improve quality for coffee growing farmers,

b) Provide evidence from appropriate regional organ about capacity and employment of appropriate professional to deliver extension services and technology support for coffee growing farmers,

c) Agree to prepare above 90% (ninty percent) of all received coffee from coffee growing farmers as specialty coffee and

d) Agree to pay above the local price for specialty coffee preparation of received coffee.

**8. <u>Importing raw coffee from abroad</u>**

1/ Raw coffee from abroad may be imported:

a) If the national significance of importing raw coffee is asserted by the study,

b) If raw coffee allowed to be imported specifies the origin of producing country and fulfills national plant health quarantine and phytosanitary certificate standard,

c) If the raw coffee to be imported uses only the permitted transport root, warehouse and processing industry,

d) If it is blended with national origin coffee by known blending ratio, and fully exported in the form of roasted or roasted and grinded or in other value added product forms,

2/ The Ethiopian Revenues and Customs Authority shall establish special customs service delivery system for raw coffee import.

https://chilot.me



**፱. ለውጪ ገበያ የተዘጋጀ ቡና በሀገር ውስጥ ስለመሸጥ**

ለውጪ ገበያ በተቆላ ወይም ተቆልቶ በተፈጨ ወይም በሌላ መልኩ የተዘጋጀ ቡና በሀገር ውስጥ ግብይት የሚፈጸመው:-

፩/ የውጪ ቡና ቆዪ ለሀገር ውስጥ ግብይት ከባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የተሰጠው እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተመዘገበ ከሆነ፣

፪/ ሽያጩ በባለሥልጣኑ ተለይተው በሚፈቀዱ አህጉርና አለም አቀፍ ኩነቶች ማካሄጃ፣ የውጪ ሀገር ጎብኚዎች መንገደኞች መተላለፊያና ማዘውተሪያ ቦታ ከሆነ፣

፫/ በአሜሪካ ዶላር ወይም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በተፈቀደ የውጭ ሀገር ገንዘብ ብቻ ሲፈጸም፣

፬/ በእሽጉ ላይ የቡናው ዓይነት፣ ስያሜ፣ የንግድ ምልክት፣ የተመረተበት ሀገር እና ለውጭ ገበያ የተዘጋጀ በሚል ከተጻፈበት፣

፭/ የተሸጠው ቡና ዓይነት፣ መጠን፣ የገንዘቡ ልክ በውጭ ምንዛሪና መሸጫ ቦታው ተገልጾ በሻጩ ለገዥው ደረሰኝ ሲሰጥ፣ እና

፮/ በየወሩ መጨረሻ ዝርዝር የቡና ግዢ እና ሽያጭ መግለጫ በሻጩ ተዘጋጅቶ በብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ ሲወራረድ እና ይኸው ለባለሥልጣኑ በሻጩ ሪፖርት ከተደረገ፣

ነው፡፡

**፲. የቡና ገለባና ቅጠል የግብይት አሠራር**

፩/ ቡና አምራች፣ የቡና ገለባ አቀነባባሪ፣ የቡና ቅጠል አቀነባባሪ ወይም ቡና ላኪ የቡና ገለባ ወይም የቡና ቅጠል በባለስልጣኑ ፈቃድ በቀጥታ ወደ ውጪ መላክ ይችላል፡፡

**9. selling of export standard coffee at domestic market**

Roasted or roasted and grinded or any other form of export coffee shall be transacted at domestic market when: -

1/ Export coffee roaster owns certificate of competence for domestic transaction from the Authority and registered at National Bank of Ethiopia.

2/ The sale is at regional and international event venues and foreign tourist travel terminals and recreational places identified and permitted by the Authority;

3/The transaction is done with U.S dollars or other foreign currency permitted only by National Bank of Ethiopia;

4/ The coffee type, brand name, trade mark, country of origin, and made for export is printed on the package;

5/ The seller provides receipt describing sold coffee type, quantity, amount of money in foreign currency and shopping place to the buyer; and

6/ At the end of each month, a detailed coffee purchase and sales statement is prepared by the seller and settled at National Bank of Ethiopia's foreign currency account, and this is reported to the Authority by the seller.

**10. Coffee husk and leaf Transaction Process**

1/ Coffee producer, coffee husk processer, coffee leave processer or coffee exporter may directly export coffee husk or coffee leaf with the permission from the Authority.

https://chilot.me



፪/ የቡና ገለባ ግብይት የሚፈጸመው ከቡና አምራች ወይም ከቡና አቅራቢ ከቡና ገለባ አቀነባባሪ ወይም ከቡና ላኪ ጋር በሚደረግ ድርድር ይሆናል፡፡

፫/ ለቡና ተክሉ ተፈጥሯዊ አገልገሎቱን ያጠናቀቀ የቡና ቅጠል ግብይት የሚፈጸመው ከቡና አምራቾች እና ፈቃድ ከተሰጣቸው የቡና ቅጠል አቀነባባሪዎች ወይም ከቡና ላኪዎች ጋር በድርድር ነው፡፡

፬/ ለሽያጭ የሚውለው የቡና ገለባ በውስጡ ያለው የቡና ፍሬ መጠን ከአንድ በመቶ መብለጥ የለበትም፡፡

፭/ ማንኛውም የቡና ገለባ ወይም የቡና ቅጠል ከቦታ ወደ ቦታ ለማዘዋወር ከባለስልጣኑ ወይም አግባብ ካለው የክልል አካል የተሰጠ መሸኛ መያዝ አለበት፡፡

፮/ ማንኛውም የቡና ገለባ ወይም የቡና ቅጠል በተቀነባበረ ወይም በጥሬው ወደ ውጭ የሚላክ ከሆነ የሽያጭ ውል ስምምነት ከተደረገ በኋላ በ፳፬ ሰዓት ውስጥ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ቀርቦ መጽደቅ እና በሦስት የሥራ ቀናት ለባለሥልጣኑ ቀርቦ መመዝገብ አለበት፡፡

፯/ በማንኛውም መልክ ወደ ውጭ የሚላክ የቡና ገለባ ወይም የቡና ቅጠል የአዘገጃጀትና ጥራት ምርመራ የምስክር ወረቀት መሸኛ ያገኘ መሆን አለበት፡፡

፲፩. <u>**የወጪ ቡና የሽያጭ ውልና አሠራር**</u>

፩/ ማንኛውም ለውጭ ገበያ ቡናን የሚያቀርብ ሰው ስለቡና ገዢው ህጋዊነት አረጋግጦ የሽያጭ ውል መፈጸም አለበት፡፡

፪/ የወጪ ቡና ሽያጭ ውል ሲፈጸም የገዢው ፍላጎት እንደተጠበቀ ሆኖ የውሉ ሰነድ:-

ሀ) የቡና ሻጭ እና ገዢ ሙሉ ስም እና የሚገኝበት አድራሻ፣

2/ The coffee husk transaction shall be made through negotiation between coffee producer or coffee supplier and coffee husk processor or coffee exporters.

3/ The transaction of coffee leaf that completed its natural life cycle shall be made through negotiation between coffee producers and coffee leaf processors or coffee exporters.

4/ Coffee bean content inside prepared coffee husk for sale should not exceed one percent.

5/ To transport any coffee husk or leaf from one place to other, dispatch from the Authority or appropriate regional organ should be held.

6/ Sales contract of any coffee husk or coffee leaf exported as processed or raw should be submitted within 24 hours to National Bank of Ethiopia and within three working days to the Authority.

7/ Coffee husk or coffee leaf exported in any form should hold processing and quality inspection certificate and dispatch.

11. <u>**Export coffee Sales Contract and process**</u>

1/ Any person supplying coffee to export market must enter into contract validating the legality of the buyer.

2/ Without prejudice to buyers demand, contract document for export coffee shall constitute the following:

a) The full name and contact address of the coffee seller and buyer,

https://chilot.me



ለ/ የቡናውን ዓይነት፣ መጠን፣ የጥራት ደረጃ፣ እና ውሉ የሚፈጸምበት ጊዜ እና የተሸጠበትን ዋጋ በአሜሪካ ዶላር፣ እና

ሐ/ ሌሎች አግባብነት ያላቸው የውል ቃሎችን መያዝ ያለበት ሲሆን ከውሉ ጋር አስፈላጊ ሰነዶች ተሟልተው ውሉ በተፈጸመ በ፳፬ ሰዓት ውስጥ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ቀርቦ መጽደቅና በሦስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ ቀርቦ መመዝገብ አለበት፡፡

፫/ የወጪ ቡና ሽያጭ ውል መፈጸሚያ ጊዜ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ከ፺ ተከታታይ ቀናት መብለጥ የለበትም፡፡

፬/ ማንኛውም የወጪ ቡና ላኪ የሽያጭ ሂሳብ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማወራረድ አለበት፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተጠቀሰው ቢኖርም ቡና ላኪው ቡና አምራች ከሆነ የውሉ መፈጸሚያ ጊዜ ከዘጠኝ ወራት ያልበለጠ ሆኖ ባመረተው ወይም በሚያመርተው የቡና ምርት ዓይነትና መጠን ልክ እስከ ቡና ምርት ዘመኑ መጨረሻ ድረስ ሊሆን ይችላል፡፡

፮/ ማንኛውም የወጪ ቡና ሽያጭ በውሉ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ፣ ጥራት፣ መጠን፣ ዋጋና ሁኔታ መሠረት መፈጸም አለበት፡፡

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) የተደነገገው ቢኖርም ውሉን ለመፈጸም የማያስችል አስገዳጅ ያልታሰበ ሁኔታ ስለመኖሩ በማስረጃና በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ከቀረበ ባለሥልጣኑ የውል ጊዜው እንዲራዘም ወይም ዋጋ በመጨመር ውሉ እንዲሻሻል ወይም ወደ ሌላ ላኪ እንዲተላለፍ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

b) Coffee type, quantity, quality grade level, and time of performance and selling price in US dollars and

c) Other contract terms; and should be submitted and approved with necessary documents within 24 hours by National Bank of Ethiopia and registered within three working days by the Authority.

3/ Coffee export contract period shall not exceed 90 consecutive days after the date of registration at National Bank of Ethiopia.

4/ Any coffee exporter should settle a sales account within the timeframe decided by the National Bank of Ethiopian.

5/ Notwithstanding to sub-article (3) of this Article, sales contract period for coffee producer may be extended up to nine month within coffee production season, according to his coffee type and quantity produced.

6/ Any export coffee sales shall be performed according to time limit, quality, quantity, price and conditions mentioned in the contract.

7/ Notwithstanding the provisions of sub-Article (6) of this Article, the Authority may extend the contract period or price premium or allow to be transferred to other coffee exporter, if there is evidence and agreement by both parties about the existence of unforeseen conditions to default a contract.

https://chilot.me



፰/ ማንኛውም ቡና ላኪ ያለበቂ ምክንያት፣ የተዋዋለውን የሽያጭ ውል በሙሉ ወይም በከፊል በተለይ በጊዜ ገደቡ ወይም በጥራት ወይም በሁለቱም ያለመፈጸሙ ሲረጋገጥ በዚህ ደንብና አግባብነት ባላቸው ህጎች አስተዳደራዊ እና ህጋዊ እርምጃ ይወሰዳል፣

፱/ ውሉን ያልፈጸመ የውጭ ሀገር ቡና ገዥ ሲኖር በውጭ ሀገር ባሉ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች አማካይነት በድርድር እንዲፈታ ይደረጋል ወይም አግባብነት ባለው ህግ እርምጃ ይወሰዳል፡፡

፲/ ማንኛውም ቡና ላኪ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከሚወሰነው አማካይ ዋጋ ዝቅተኛ ህዳግ በታች ወይም ብሔራዊ ጥቅምን የሚያሳጣ ተደጋጋሚ የሽያጭ ውል ማስመዝገቡ ሲረጋገጥ በዚህ ደንብና አግባብነት ባላቸው ህጎች አስተዳደራዊ እና ህጋዊ እርምጃ ይወሰዳል፡፡

፲፩/ ማንኛውም ቡና አምራች ወይም ቡና ላኪ የኢትዮጵያን ቡና ልዩ ተፈጥሯዊ ጣዕምና ባህሪይ ለማስተዋወቅና የተሻለ ዋጋ ለማስገኘት በውጭ ሀገር የተጠቃሚ ገበያ በቀጥታ ወይም በህጋዊ ሽርክና በገበያ ለመሳተፍ የፈለገ እንደሆነ ሀገራዊ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው በጥናት ተረጋግጦ ባለሥልጣኑ ሊፈቀድ ይችላል፡፡

**፲፪. <u>ለውጭ ሀገር ገዢ የውጪ ቡናን በሀገር ውስጥ ስለማስረከብ</u>**

፩/ ለውጭ ሀገር ቡና ገዢ የተሸጠ የውጪ ቡና በሀገር ውስጥ ርክክብ እንዲፈጸምና ለተወሰነ ጊዜ እንዲከማች ሀገራዊ ፋይዳው በጥናት ሲረጋገጥ በባለሥልጣኑ ሊፈቀድ ይችላል፡፡

፪/ ማንኛውም የውጭ ሀገር ቡና ግዢ በሀገር ውስጥ የቡና ርክክብ የሚፈጽመው አስቀድሞ በውል ስምምነቱ ከተገለጸ ነው፡፡

8/ Any coffee exporter without sufficient ground, fully or partially defaults the sales contract he entered, especially in time limit or in quality or in both, legal and administrative measures shall be taken.

9/ When there is a default of contract by foreign coffee buyer, it may be resolved through negotiation using Ethiopian embassies or legal measures shall be taken.

10/ When any coffee exporter frequently registers below the average price range decided by National Bank of Ethiopia or loss of national interest is proved, administrative and legal measures shall be taken based on this regulation and other relevant laws.

11/ If any coffee producer or coffee exporter wants to involve in direct foreign marketing or legal partnership to promote the natural taste and characteristics of Ethiopia special coffee and obtain better price for such, the authority may permit, when its national economic significance is asserted by a study.

**12. <u>Domestic delivery of Export coffee to foreign buyer</u>**

1/ When the national significance is verified by a study, export coffee sold to foreign buyer may be delivered domestically and stored for a limited time by the permission of the Authority.

2/ Any foreign coffee buyer may receive coffee domestically, when such term is mentioned in the contract initially.

https://chilot.me



፫/ የውጭ ሀገር ቡና ገገር በሀገር ውስጥ የወጪ ገበያ ቡናን ከተረከበበት ቀን ቀጥሎ ባሉት ሦስት የሥራ ቀናት ውስጥ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በተመዘገበ የሽያጭ ውል መሠረት ክፍያ መፈጸም አለበት፡፡

፬/ የውጭ ሀገር ቡና ገዥ በሀገር ውስጥ የተረከበውን ቡና አስፈላጊውን የሎጀስቲክና የሽኝት ሥነ ሥርዓት አጠናቆ ወደ ወደብ ሊያጓጓዝ ወይም በተፈቀደለት ጥብቅ የቡና ማከማቻ መጋዘን እስከ ሦስት ወራት አከማችቶ ሊያቆይ ይችላል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፬) የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም የውጭ ሀገር ቡና ገዢ ቡናውን ወደ ወደብ ማጓጓዝ የሚችለው ከባለሥልጣኑ በጽሁፍ የተረጋገጠ ፈቃድ እና የጉምሩክ ሽኝት አገልግሎት ሲያገኝ ብቻ ነው፡፡

፮/ በማናቸውም ምክንያቶች የውጪ ሀገር ቡና ገዥ የተረከበውን ቡና በሀገር ውስጥ መልሶ መሸጥ አይችልም፡፡

## ክፍል ሦስት
## የቀይ እሸት እና ጀንፈል ቡና መገበያያ ስፍራ እና አስተዳደር

**፲፫. የመገበያያ ስፍራ እና አሰራር ስለመወሰን**

፩/ አግባብ ያለው የክልል አካል የቀይ እሸትና የጀንፈል ቡና መገበያያ ስፍራን፣ ወሰንን፣ ብዛትንና ስርጭትን ይወስናል፣ ይከልላል፣ የአስተዳደር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

፪/ አግባብ ያለው የክልል አካል የመገበያያ ስፍራ፣ ወሰን፣ ብዛትና ስርጭት ሲወስንና ሲከልል:-

ሀ) የቡና አምራች አርሶ አደሮችን ብዛት፣

ለ) በቡና የተሸፈነ ማሳ መጠንን፣

3/ foreign coffee buyer within three working days after the date he received export coffee, shall pay according to the registered sales contract at National Bank of Ethiopia.

4/ A foreign coffee buyer after finishing the necessary logistics and dispatch procedures may transport to port or store up to three months at permitted bonded coffee warehouse.

5/ Notwithstanding the provisions of sub-article (4) of this article, any foreign buyer shall only transport to the port with written permission from the Authority and custom delivery notes.

6/ Foreign coffee buyer shall not re-sale received coffee for any reason at domestic market.

## SECTION THREE
## RED CHERRY AND COFFEE WITH PULP TRANSACTION PLACE AND ADMINSTRAION

**13. Determination and administration of transaction places**

1/ The appropriate regional organ shall determine and demarcate places, dimensions, number and distribution of red cherry and coffee with pulp transaction places and establish administration system.

2/ When appropriate regional organ decides transaction places, number and distribution, should consider:

a) Number of coffee growing farmers,

b) Area of coffee plantation,

https://chilot.me



ሐ) የህዝቡን አሰፋፈርና የመሬቱን አቀማመጥ፣

መ) ለአምራች አርሶ አደሮች የቡና ምርታቸውን ለማቅረብ ያላቸውን አንጻራዊ ቀረቤታና ለተገበያዮቹ የግብይት እንቅስቃሴ አመቺ ነት፣ እና

ሠ) የቡና ጥራትን ለማስጠበቅ የሚኖራቸውን አስተዋጽኦ፤

ከግምት ውስጥ መግባት ይኖርበታል፡፡

፫/ የአቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ለቀይ እሸትና ጀንፈል ቡና መገበያያነት እንዲያገለግል የተወሰነ ከሆነ ለግብይት የተለየ ቦታ፣ የቡና ጥራት ጉድለት መልቀሚያ አልጋ፣ ለጋማ ከብቶች ማቆያ የተለየ ቦታ፣ ዕለታዊ የቡና ገበያ ዋጋ ማሳወቂያ ሠሌዳ፣ የደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያ እና መፀዳጃ ቤት ማሟላት አለበት፡፡

፬/ የአቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ተደራሽ ባልሆኑባቸው ወይም በሌሉባቸው አከባቢዎች ለቀይ እሸትና ጀንፈል ቡና መገበያያነት እንዲያገለግል የተወሰነው የመጀመ ሪያ ደረጃ ቡና ግብይት ማዕከል ከሆነ:-

ሀ) ለቡና አምራች አርሶ አደሩ ቀረቤታ፣

ለ) ለግብይቱ የሚሆን ቢያንስ ፶ ሜትር በ፶ ሜትር ስፋት ያለው የታጠረ ቦታ፣

ሐ) የቡና ጥራት ጉድለት መልቀሚያ አልጋ፣

መ) ለጋማ ከብቶች ማቆያ የተለየ ቦታ፣

ሠ) ዕለታዊ የቡና ገበያ ዋጋ ማሳወቂያ ሠሌዳ፣

ረ) ደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያ እና መፀዳጃ ቤት፣ እና

ሰ) በእያንዳንዱ ቡና አቅራቢ ስም ወለሉ በሲሚንቶ የተሠራ የምርት ግገር መፈፀሚያ ክፍል፣

ያለው መሆን ይኖርበታል፡፡



c) Population, settlement and land topography,

d) Relative proximity to growing farmers for supplying their coffee and its convenience to transacting actors for marketing process, and

e) Importance for maintaining coffee quality.

3/ When supply coffee processing and warehousing industry is decided to serve as transacting center for red cherry coffee and coffee with pulp, should have separate transacting place, coffee defect sorting bed to identify quality, parking place for transport animals, daily market information ticker board, dry waste disposal and pit latrine.

4/ where supply coffee processing industries are inaccessible or not existent at such localities, first level coffee transaction center decided to be transaction center for red cherry coffee and coffee with pulp should have:

a) Proximity for coffee growing farmers,

b) At least 50 meter by 50 meter dimension and fenced place,

c) Coffee quality Sorting bed,

d) Special parking place for transport animals,

e) Daily market price information ticker board,

f) Dry waste disposal and pit latrine, and

g) Transaction room with cemented floor in the name of each supplier.

https://chilot.me



፭/ ቡና አምራች አርሶ አደር የተሻለ የቡና ዋጋ በሚያስገኝለት ኢንዱስትሪ ወይም የመጀመሪያ ደረጃ ገበያ መርጦ መሸጥ ይችላል፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም በልማትና ግብይት የተሳሰሩ አልሚ ባለሃብቶች እና በአምራችና ኢንዱስትሪ የሚተሳሰሩ የወጪ ቡና ቆዪ ኢንዱስትሪዎች ከቡና አምራች አርሶ አደሮች የሚረከቡት ቀይ እሸት ወይም ጀንፈል ቡና በውል ስምምነታቸው በተገለጸው ስፍራ ይሆናል፡፡

፯/ አግባብ ያለው የክልል አካል የቀይ እሸትና ጀንፈል ቡና መገበያያ ስፍራ በቡና ጥራትና ግብይት ሂደቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ከሚያሳድሩ ነገሮች ነፃ መሆኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ እርምጃ ይወስዳል፡፡

፲፬. የቀይ እሸት እና የጀንፈል ቡና ግብይት ወቅት

፩/ በአቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪም ሆነ በመጀመሪያ ደረጃ የቡና ግብይት ማዕከላት ግብይቱ የሚጀምርበትና የሚጠናቀቅበት ወቅት አግባብ ባለው የክልል አካል ይወሰናል፡፡

፪/ በአቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪዎች ሆነ በመጀመሪያ ደረጃ የቡና ግብይት ማዕከላት የሚፈጸመው ግብይት ወይም በውል ስምምነት መሰረት የሚፈጸም ርክክብ ከጠዋቱ ፫ ሰዓት እስከ ምሽቱ ፲፪ ሰዓት ብቻ መሆን ይኖርበታል፣

## ክፍል አራት

## የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

### ፲፭. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አስፈላጊነት

የአዋጁ አንቀጽ ፰(፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሰው የቡና ግብይትን ለማከናወን፣ ቡናን ለማዘጋጀት፣ ለማከማቸት፣ እሴት ለመጨመር፣ ለማሸግ፣ ለማጓጓዝ እና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው

5/ Coffee growing farmer may choose to sell either primary market center or industry where better price is paid.

6/ Notwithstanding sub-article (1) of this Article, commercial coffee growers who established out growers scheme and export coffee roasters who established coffee grower industry linkage shall receive red cherry coffee or coffee with pulp from coffee growing farmers at the place specified in their agreement.

7/ Appropriate Regional organ shall monitor, regulate and take measures on red cherry and coffee with pulp marketing places to make sure that it is free from conditions which negatively affect coffee quality and marketing process.

**14. Transaction Season of red cherry and coffee with pulp**

1/ The beginning and ending time of transaction, either at supply coffee processing industries or at first level coffee transaction centers, shall be determined by appropriate regional organ.

2/ The trading hours either at supply coffee processing and warehousing industry or first level coffee transaction centers or delivery should be from 3 o'clock in the morning up to 12 o'clock in the evening at local time.

## SECTION FOUR

## CERTIFICATE OF COMPETENCE

### 15. The Certificate of Competence

Without prejudice to article 8(1) of the proclamation any person engaging in coffee transaction, processing, storing, value adding, packaging, transporting and providing other

https://chilot.me



አገልግሎቶችን ለመስጠት በዚህ ደንብ መሰረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው መሆን ይኖርበታል፡፡

## ንዑስ ክፍል አንድ

## ስለብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ዓይነቶችና መስፈርቶች

**፲፮. የቡና ልማትና ግብይት ትስስር ለሚፈጥር አልሚና ላኪ የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ**

ማንኛውም ሰው ለቡና አልሚና ላኪ የልማትና ግብይት ትስስር ለመፍጠር የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው:-

፩/ የቡና ልማት ኢንቨስትመንት ፈቃድ እና የመሬት ሊዝ ውል ያለው፣

፪/ በቡና የተሸፈነ መሬትና ዘመናዊ የቡና ልማት በማካሄድ የተሻሻለ ምርታማነትና የምርት ጥራት ደረጃ ስለመድረሱ ማስረጃ ያለው፣

፫/ ለአምራች አርሶ አደሮች ዘመናዊ የቡና አመራረት ዘዴ ለማስፋፋት የቡና ዕውቀትና ክህሎት ያለውን ባለሙያ ማሰማራቱን የሚገልጽ ማስረጃ ያለው፣

፬/ ለአምራች አርሶ አደሮች ዘመናዊ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ድጋፍ እና የተሻሻሉ ግብዓቶችን በማቅረብ ምርታማነትና የምርት ጥራት ለማሻሻል የተስማማ፣

፭/ ከአምራች አርሶ አደሮች ለሚረከበው ቡና ከአካባቢው ወቅታዊ የገበያ ዋጋ የተሻለ ለመክፈል የተስማማ፣

፮/ ከቡና አልሚ ባለሃብት ማሳ ኩታገጠም ወይም በቅርብ ርቀት የሚገኙ ቡና አምራች አርሶ አደሮችን ዝርዝርና በእያንዳንዱ አርሶ አደር በባለቤትነት የተመዘገበ በቡና የተሸፈነ ማሳ መጠንና ከዚሁ የሚገኝ ዓመታዊ የምርት መጠን የሚገልጽ ማስረጃ እና አርሶ አደሮቹ ስለመብትና ግዴታቸው ተወያይተው የተፈራረሙበት የቃለ ጉባኤ ሰነድ ያለው፣ እና

related services shall have a certificate of competence in accordance with this Regulation.

## Sub-section One

## Types and Criteria of Certificate of Competence

**16. Certificate of competence to establish out growers scheme for producer and exporters**

Certificate of competence to establish out grower scheme for coffee producers and exporters shall be issued, when any person:

1/ Holds coffee development investment license and land lease;

2/ Provides evidence for coffee plantation land and achievement of improved productivity and product quality by implementing modern coffee development;

3/ Provides evidence about employment of professional with coffee knowledge and skill to promote modern coffee farming methods for coffee growing farmers;

4/ Agrees to provide modern extension service support and improved farm inputs to improve productivity and product quality for coffee growing farmers ;

5/ Agrees to pay better price than locally existing market price for received coffee from coffee growing farmers,

6/ Holds evidence for coffee growing farmers' list clustered or nearby, area of coffee plantation by each farmer and its annual yield and signed document of discussed minutes on rights and obligations of the coffee growing farmers; and

https://chilot.me



፯/ በባለቤትነት የተያዘ ወይም በተመዘገበ የኪራይ ውል ያገኘው የቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ያለው ስለመሆኑ ማስረጃ ያለው፣ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

፲፯. <u>የቡና አቅራቢነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት</u>

ማንኛውም ሰው የቡና አቅራቢነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው:-

፩/ በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ሲሆን የሥራ አድራሻ ያለው፤ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ ቋሚ ንብረት እና የመኖሪያ አድራሻ ያለው፤

፪/ በማንኛውም ንግድ ወይም በማህበራዊ አገልግሎት ወይም በተሠማራበት የሙያ መስክ መልካም አፈጻጸምና ስም ያለው ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማምጣት የሚችል፤

፫/ አግባብ ባለው የክልል አካል የተዘጋጀውን የቴክኒክ መስፈርት ያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይም አግባብ ባለው አካል በጸደቀ የኪራይ ውል ያገኘዉ የታጠበ ወይም ያልታጠበ የአቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ያለው፤

፬/ አግባብ ባለው የመንግሥት ተቋም በዘመኑ የተመረመረ ሚዛንና የእርጥበት መለኪያ መሣሪያ ያለው፤

፭/ ስለ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪው አሠራር ሁኔታ ከሚመለከተው መንግሥታዊ አካል የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ ማቅረብ የሚችል፤

፮/ ከቡና ግብይት፣ ክምችት፣ አዘገጃጀትና ጥራት አያያዝ ጋር በተያያዘ ዕውቀትና ክህሎት ያለው ባለሙያ በቋሚነት የቀጠረ፤

፯/ የአቅርቦት ቡና አዘገጃጀትን በሚመለከት አግባብ ባለው የክልል አካል በተቀመጡ መስፈርቶች መሠረት ለማዘጋጀት የተስማማ፤

7/ Holds evidence of ownership or registered lease contract for coffee processing and warehousing industry.

17. <u>Coffee Suppliers Certificate of Competence</u>

The coffee supplier's certificate of competence shall be issued, when any person:

1/ Has a business address for a juridical person; has fixed asset and residence address for a natural person;

2/ Provides evidence from relevant organ about good performance and reputation of any business work or social service or professional engagement;

3/ Owns or has leased through approved contract by Authorized organ a washed and unwashed coffee processing and warehousing industry which meets technical standards issued by the appropriate regional organ;

4/ Owns weighing scale and moisture calibrator verified by the appropriate governmental organ;

5/ Provides environmental impact assessment document on processing and warehousing industries from the appropriate government organ;

6/ Employs permanently, professionals with knowledge and skill about coffee transaction, storing, processing and quality management;

7/ agrees to process supply coffee according to standards set by the appropriate regional organ;

https://chilot.me


፰/ ስለቡና ግዥ፣ ዝግጅት፣ ክምችትና ሽያጭ መረጃ ለማደራጀት እና መረጃውን አግባብ ባለው አስፈጻሚ አካል በተጠየቀ ጊዜ ለመስጠት የተስማማ፤

፱/ በአቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪው የሚዘጋጅ ቡና ግዥ በህጋዊ ግብይት ብቻ ስለመከናወኑ ሙሉ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ አውቆ የተስማማ፤ እና

፲/ በቡና ንግድ በወንጀል ወይም በአስተዳደር ቅጣት ተወስኖበት ከነበረ ቅጣቱን የፈጸመ ወይም የወንጀል ቅጣቱ የተገደበለት ከሆነ ገደቡን የፈጸመ፤

መሆኑ ሲረጋገጥ ይሆናል፡፡

## ፲፰. የቡና ላኪነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት

ማንኛውም ሰው የቡና ላኪነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው:-

፩/ በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ሲሆን የሥራ አድራሻ ያለው፤ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ ቋሚ ንብረት እና የመኖሪያ አድራሻ ያለው፤

፪/ በማንኛውም ንግድ ወይም በማህበራዊ አገልግሎት ወይም በተሠማራበት የሙያ መስክ መልካም አፈጻጸምና ስም ያለው ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማምጣት የሚችል፤

፫/ በባለስልጣኑ የተዘጋጀውን የቴክኒክ መስፈርት ያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይም ስልጣን ባለው አካል በጸደቀ ውል ከሦስተኛ ወገን ያገኘው ወይም የአገልግሎት ውል ያለው የወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ያለው፤

፬/ አግባብ ባለው የመንግሥት ተቋም በዘመኑ የተመረመረ ሚዛንና የእርጥበት መለኪያ መሣሪያ ያለው፤

8/ Organizes coffee purchase, process, sells and stock information and agrees to provide for relevant executing organ upon request;

9/ Agrees to take full responsibility about the legality of the transaction of the purchased coffee to be processed in his coffee processing and warehousing industry; and

10/ If criminally or administratively convicted in coffee trade, completes the punishment, if criminal punishment is Suspended, completes the suspension.

## 18. Coffee exporter's certificate of competence

The coffee exporter's certificate of competence shall be issued, when any person:

1/ Has a business address for a juridical person; has fixed asset and residence address for a natural person;

2/ Provides evidence from relevant organ about good performance and reputation of any business work or social service or professional engagement;

3/ Owns or has leased or has service contract through contract approved by Authorized organ from a third party an export coffee processing and warehousing industry which meets technical standards issued by the Authority;

4/ Owns weighing scale and moisture calibrator verified by the appropriate governmental organ;

https://chilot.me



፭/ ስለ ወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪው አሠራር ሁኔታ ከሚመለከተው መንግሥታዊ አካል የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ ማቅረብ የሚችል፤

፮/ ከቡና ግብይት፣ ክምችት፣ አዘገጃጀትና ጥራት አያያዝ ጋር በተያያዘ ዕውቀትና ክህሎት ያለው ባለሙያ በቋሚነት የቀጠረ፤

፯/ በህግ የሀገሪቱን የወጪ ቡና የጥራት ደረጃ ለማስጠበቅ የተቀመጡ ግዴታዎችን እና መስፈርቶችን ጠብቆና ብሔራዊ ጥቅምን ከሚጎዳ ተግባር ተቆጥቦ ለመሥራት የተስማማ፤

፰/ ስለቡና ግዥ፣ ዝግጅት፣ ክምችትና ሽያጭ መረጃ በማደራጀት መረጃውን አግባብ ባለው አስፈጻሚ አካል በተጠየቀ ጊዜ ለመስጠት የተስማማ፤

፱/ የወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪው የሚዘጋጅ ቡና ግዥ በህጋዊ ግብይት ብቻ መከናወኑን ሙሉ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ አውቆ የተስማማ፤ እና

፲/ በቡና ንግድ በወንጀል ወይም በአስተዳደር ቅጣት ተወስኖበት ከነበረ ቅጣቱን የፈጸመ ወይም የወንጀል ቅጣቱ የተገደበለት ከሆነ ገደቡን የፈጸመ፤

መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

## ፲፱. የወጪ ቡና ቆዪነት የብቃት ማረጋገጫ

ማንኛውም ሰው የወጪ ቡና ቆዪነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው:-

፩/ በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ሲሆን የሥራ አድራሻ ያለው፤ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ ቋሚ ንብረት እና የመኖሪያ አድራሻ ያለው፤

5/ Provides environmental impact assessment document on export coffee processing and warehousing industries from the appropriate government organ;

6/ Employs permanently professionals with knowledge and skill about coffee transaction, storing, processing and quality management;

7/ Agrees to work with the national export coffee quality standard set by a law and restrains from harming national interest;

8/ Organizes coffee purchase, process, sells and stock information and agrees to provide for the appropriate executing organ upon request;

9/ Agrees to take full responsibility about the legality of the transaction of the purchased coffee to be processed in his export coffee processing and warehousing industry; and

10/ if criminally or administratively convicted in coffee trade, completes the punishment; if criminal punishment is Suspended, completes the suspension.

## 19. Export Coffee Roaster's Certificate of Competence

The export coffee roaster's certificate of competence shall be issued, when any person:

1/ Has a business address for a juridical person; has fixed asset and residence address for a natural person;

https://chilot.me



፪/ በማንኛውም ንግድ ወይም በማህበራዊ አገልግሎት ወይም በተሠማራበት የሙያ መስክ መልካም አፈጻጸምና ስም ያለው ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማምጣት የሚችል፤

፫/ በባለስልጣኑ የተዘጋጀውን የቴክኒክ መስፈርት ያሟሉ በባለቤትነት የያዛቸው ወይም አግባብ ባለው አካል በጸደቀ ውል በኪራይ ያገኛቸው እሴት የተጨመረበት የወጪ ቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ እና የቡና ጥራትና ጣዕም ምርመራ ላብራቶሪ ያለው፤

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በተፈቀዱ መገበያያ ስፍራዎች ቀይ እሸት ወይም ጀንፈል ቡና የሚገዛ ከሆነ በባለቤትነት የያዘው ወይም ከሦስተኛ ወገን በኪራይ ውል ያገኘው የአቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ያለው፤

፭/ ስለ ወጪ ቡና እሴት የሚጨምር ማዘጋጃ ኢንዱስትሪውን በሚመለከት በሚመለከተው መንግሥታዊ አካል የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ ማቅረብ የሚችል፤

፮/ በህግ የሀገሪቱን የወጪ ቡና የጥራት ደረጃ ለማስጠበቅ የተቀመጡ ግዴታዎችንና መስፈርቶችን ጠብቆና ብሔራዊ ጥቅምን ከሚጎዳ ተግባር ተቆጥቦ ለመሥራት የተስማማ፤

፯/ ከቡና ግብይት፣ ክምችት፣ አዘገጃጀት፣ እሴት ጭመራና ጥራት አያያዝ ጋር በተያያዘ ዕውቀትና ክህሎት ያለው ባለሙያ በቋሚነት የቀጠረ፤

፰/ ለአዘጋጀው እሴት የተጨመረበት ቡና የራሱ የሆነ ስያሜ እና የንግድ ምልክት ያለው፤

፱/ እያንዳንዱን የቡና ዓይነት ተፈጥሯዊ ባህሪውን ጠብቆ ወይም በሚታወቅ የቅይጥ ምጣኔ ጥንቅር እሴት የተጨመረበት የወጪ ገበያ ቡና አዘጋጅቶ ወደ ውጭ ለመላክ የተስማማ፤

2/ Provides evidence from relevant organ about good performance and reputation of any business work or social service or professional engagement;

3/ Owns or has leased through approved contract by Authorized organ value added export coffee processing industry and a coffee liquoring laboratory which meets technical standards issued by the Authority;

4/ Without prejudice to the provisions of sub-Article (3) of this Article, owns or has leased through contract from third party a supply coffee processing and warehousing industries, if red chary or coffee with pulp purchased from permitted transaction places;

5/ Provides environmental impact assessment document from relevant government organ about value added export coffee processing industries;

6/ Agrees to work with the national export coffee quality standard obligation set by a law and restrains from harming national interest;

7/ Employs permanently professional with knowledge and skill about coffee transaction, storing, processing, value adding and quality management;

8/ has its own trade mark and brand name for his prepared value added coffee;

9/ Agrees to process and export value added export coffee by maintaining the natural characteristics and official blending for each coffee type while processing;

https://chilot.me



፲/ ስለቡና ግዥ፣ ክምችት፣ ዝግጅት፣ እሴት ጭመራና ሽያጭ መረጃ ለማደራጀት እና መረጃውን አግባብ ባለው አስፈጻሚ አካል በተጠየቀ ጊዜ ለመስጠት የተስማማ፤

፲፩/ እሴት በሚጨምር የወጪ ቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪው ውስጥ የሚዘጋጅ ቡና ግዥ በህጋዊ ግብይት ብቻ መከናወኑን ሙሉ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ አውቆ የተስማማ፣ እና

፲፪/ በቡና ንግድ በወንጀል ወይም በአስተዳደር ቅጣት ተወስኖበት ከነበረ ቅጣቱን የፈጸመ ወይም የወንጀል ቅጣቱ የተገደበለት ከሆነ ገደቡን የፈጸመ፤

መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

**፳. <u>የሀገር ውስጥ ቡና ቆዪነት የብቃት ማረጋገጫ</u>**

ማንኛውም ሰው ለሀገር ውስጥ ቡና ቆዪነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው:-

፩/ በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ሲሆን የሥራ አድራሻ ያለው፤ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ ቋሚ ንብረት እና የመኖሪያ አድራሻ ያለው፤

፪/ በማንኛውም ንግድ ወይም በማህበራዊ አገልግሎት ወይም በተሠማራበት የሙያ መስክ መልካም አፈጻጸምና ስም ያለው ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማምጣት የሚችል፤

፫/ በባለስልጣኑ የተዘጋጀውን የቴክኒክ መስፈርት ያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይም አግባብ ባለው አካል በጸደቀ ውል በኪራይ ያገኘው እሴት የሚጨር የሀገር ውስጥ ገበያ ቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ እና የቡና ጥራትና ጣዕም ምርመራ ላብራቶሪ ያለው፤

፬/ ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና እሴት የሚጨምር ማዘጋጃ ኢንዱስትሪው ከሚመለከተው መንግሥታዊ አካል የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ ማቅረብ የሚችል፤

፭/ ከቡና ግብይት፣ ክምችት፣ አዘገጃጀት፣ እሴት ጭመራና ጥራት አያያዝ ጋር በተያያዘ ዕውቀትና ክህሎት ያለው ባለሙያ በቋሚነት የቀጠረ፤

10/ Organizes coffee purchase, process, value addition, sells and stock information and agrees to provide for relevant executing organ upon request;

11/ Agrees to take full responsibility about the legality of the transaction of the purchased coffee to be processed in his value adding export coffee processing industry; and

12/ if criminally or administratively convicted in coffee trade, Completes the punishment; if criminal punishment is Suspended, completes the suspension.

**20. <u>Domestic Coffee roaster's Certificate of Competence</u>**

The domestic coffee roaster's certificate of competence shall be issued, when any person:

1/ Has a business address for a juridical person; has fixed asset and residence address for a natural person;

2/ Provides evidence from relevant organ about good performance and reputation of any business work or social service or professional engagement;

3/ Owns or has leased through approved contract by Authorized organ value added domestic consumption coffee processing industry and a coffee liquoring laboratory which meets technical standards issued by the Authority;

4/ Provides environmental impact assessment document from relevant government organ about value added domestic consumption coffee processing industries;

5/ Employs permanently professionals with knowledge and skill about coffee transaction, storing, processing, value adding and quality management;

https://chilot.me



፮/ ለአዘጋጀው እሴት የተጨመረበት ቡና የራሱ የሆነ ስያሜ እና የንግድ ምልክት ያለው፤

፯/ እያንዳንዱን የቡና ዓይነት ተፈጥሯዊ ባህሪውን ጠብቆ ወይም በሚታወቅ የቅይጥ ምጣኔ ጥንቅር አዘጋጅቶ እሴት የተጨመረ ቡና ለሀገር ውስጥ ገበያ ለማቅረብ የተስማማ፤

፰/ ስለቡና ግዥ፣ ክምችት፣ ዝግጅት፣ እሴት ጭመራና ሽያጭ መረጃ ለማደራጀት እና መረጃውን አግባብ ባለው አስፈጻሚ አካል በተጠየቀ ጊዜ ለመስጠት የተስማማ፤

፱/ እሴት በሚጨምር የሀገር ውስጥ ቡና ማዘጋጀ ኢንዱስትሪው ውስጥ የሚዘጋጅ ቡና ግዥ ሆነ ሽያጭ ቡና በህጋዊ ግብይት ብቻ መከናወኑን ሙሉ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ አውቆ የተስማማ፤ እና

፲/ በቡና ንግድ በወንጀል ወይም በአስተዳደር ቅጣት ተወስኖበት ከነበረ ቅጣቱን የፈጸመ ወይም የወንጀል ቅጣቱ የተገደበለት ከሆነ ገደቡን የፈጸመ፤

መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

## ፳፩. የወጪ ቡና አዘጋጅነትና ማከማቸት አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ

ማንኛውም ሰው የወጪ ቡና አዘጋጅነትና ማከማቸት አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው:-

፩/ በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ሲሆን የሥራ አድራሻ ያለው፤ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ ቋሚ ንብረት እና የመኖሪያ አድራሻ ያለው፤

፪/ በማንኛውም ንግድ ወይም በማህበራዊ አገልግሎት ወይም በተሠማራበት የሙያ መስክ መልካም አፈጻጸምና ስም ያለው ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማምጣት የሚችል፤

6/ Has its own trade mark and brand name for his prepared value added coffee;

7/ Agrees to process and supply value added domestic consumption coffee by maintaining the natural characteristics and official blending for each coffee type while processing;

8/ Organizes coffee purchase, process, value addition, sells and stock information and agrees to provide for relevant executing organ upon request;

9/ Agrees to take full responsibility about the legality of the transaction of the purchased coffee to be processed in his value adding domestic consumption coffee processing industry; and

10/ if criminally or administratively convicted in coffee trade, Completes the punishment; if criminal punishment is Suspended, completes the suspension.

## 21. Export coffee processing and warehouse service provider's Certificate of Competence

The export coffee processing and warehouse service provider's certificate of competence shall be issued, when any person:

1/ Has a business address for a juridical person; has fixed asset and residence address for a natural person;

2/ Provides evidence from relevant organ about good performance and reputation of any business work or social service or professional engagement;

https://chilot.me



፫/ በባለስልጣኑ የተዘጋጀውን የቴክኒክ መስፈርት ያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይም አግባብ ባለው አካል በጸደቀ ኪራይ ውል ያገኘው የወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ እና የቡና ጥራትና ጣዕም ምርመራ ላቦራቶሪ ያለው፤

፬/ ስለወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪው በሚመለከተው መንግሥታዊ አካል የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ ማቅረብ የሚችል፤

፭/ ከቡና ግብይት፣ ክምችት፣ አዘገጃጀትና ጥራት አያያዝ ጋር በተያያዘ ዕውቀትና ክህሎት ያለው ባለሙያ በቋሚነት የቀጠረ፤

፮/ በህግ የሀገሪቱን የወጪ ቡና የጥራት ደረጃ ለማስጠበቅ የተቀመጡ ግዴታዎችንና መስፈርቶችን ጠብቆና ብሔራዊ ጥቅምን ከሚጎዳ ተግባር ተቆጥቦ ለመሥራት የተስማማ፤

፯/ የተለያዩ ባህሪ ወይም ደረጃ ያላቸውን የቡና ዓይነቶች ለይቶ ለማዘጋጀትና ለማከማቸት የሚያስችለው አሠራር ያለው፤

፰/ ስለቡና ግዥ፣ ዝግጅት፣ ክምችትና ሽያጭ መረጃ ለማደራጀት እና መረጃውን አግባብ ባለው አስፈጻሚ አካል በተጠየቀ ጊዜ ለመስጠት የተስማማ፤

፱/ በወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪው የሚዘጋጅ ቡና በህጋዊ ግብይት ብቻ መከናወኑን ሙሉ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ አውቆ የተስማማ፤ እና

፲/ በቡና ንግድ በወንጀል ወይም በአስተዳደር ቅጣት ተወስኖበት ከነበረ ቅጣቱን የፈጸመ ወይም የወንጀል ቅጣቱ የተገደበለት ከሆነ ገደቡን የፈጸመ፤

መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

3/ Owns or has leased through approved contract by Authorized organ export coffee processing and warehousing industry and a coffee liquoring laboratory which meets technical standards issued by the Authority;

4/ Provides environmental impact assessment document from relevant government organ about export coffee processing and warehousing industries;

5/ Employs permanently professionals with knowledge and skill about coffee transaction, storing, processing, value adding and quality management;

6/ Agrees to work with the national export coffee quality standards set by a law and restrains from harming national interest,

7/ Has operational procedures to process and store by identifying different characteristics and grades of coffee types;

8/ Organizes coffee purchase, process, sells and stock information and agrees to provide for relevant executing organ upon request;

9/ Agrees to take full responsibility about the legality of the transaction to be processed in his export coffee processing and warehousing industry; and

10/ if criminally or administratively convicted in coffee trade, completes the punishment; if criminal punishment is Suspended, completes the suspension.

https://chilot.me



**፳፪. የአቅርቦት ቡና ማዘጋጀትና ማከማቸት አገልግሎት ሰጪነት የብቃት ማረጋገጫ**

ማንኛውም ሰው የአቅርቦት ቡና ማዘጋጀትና ማከማቸት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው:-

፩/ በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ሲሆን የሥራ አድራሻ ያለው፣ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ ቋሚ ንብረት እና የመኖሪያ አድራሻ ያለው፤

፪/ በማንኛውም ንግድ ወይም በማህበራዊ አገልግሎት ወይም በተሠማራበት የሙያ መስክ መልካም አፈጻጸምና ስም ያለው ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማምጣት የሚችል፤

፫/ በባለስልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል የተዘጋጀውን የቴክኒክ መስፈርት ያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይም አግባብ ባለው አካል የጸደቀ ኪራይ ውል ያገኘው የአቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ያለው እና የቡና እርጥበት መለኪያ ያለው፤

፬/ ለቡና አምራቾች ብቻ ቡና የማዘጋጀትና የማከማቸት አገልግሎት ውል ለመስጠት የተስማማ፤

፭/ በሚመለከተው መንግሥታዊ አካል የተረጋገጠ ስለማዘጋጃ ኢንዱስትሪው የሥራ እንቅስቃሴ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ ማቅረብ የሚችል፤

፮/ ከቡና ግብይት፣ ክምችት፣ አዘገጃጀትና ጥራት አያያዝ ጋር በተያያዘ ዕውቀትና ክህሎት ያለው ባለሙያ በቋሚነት የቀጠረ፤

፯/ በህግ የሀገሪቱን የወጪ ቡና የጥራት ደረጃ ለማስጠበቅ የተቀመጡ ግዴታዎችንና መስፈር ቶችን ጠብቆና ብሔራዊ ጥቅምን ከሚጎዳ ተግባር ተቆጥቦ ለመሥራት የተስማማ፤

፰/ የተለያዩ ባህሪ ወይም ደረጃ ያላቸውን የቡና ዓይነቶች ለይቶ ለማዘጋጀትና ለማከማቸት የሚያስችለው አሠራር ያለው፤

**22. Supply coffee processor's and warehouse service provider's Certificate of Competence**

The Supply coffee processor's and warehouse service provider's Certificate of Competence shall be issued, when any person:

1/ Has a business address for a juridical person; has fixed asset and residence address for a natural person;

2/ Provides evidence from relevant organ about good performance and reputation of any business work or social service or professional engagement;

3/ Owns or has leased through approved contract by Authorized organ a supply coffee processing and warehousing industry and coffee moisture scale which meets technical standards issued by the Authority or appropriate regional organ;

4/ Agrees to Provide processing and warehousing service only for coffee producers;

5/ Provides environmental impact assessment document from the appropriate government organ about export coffee processing and warehousing industries;

6/ Employs permanently professionals with knowledge and skill about coffee transaction, storing, processing, value adding and quality management;

7/ Agrees to work with the national export coffee quality standard set by a law and restrains from harming national interest;

8/ Has operational procedures to process and store by identifying different characteristics and grades of coffee types;

https://chilot.me



፱/ ስለቡና ግዥ፣ ዝግጅት፣ ክምችትና ሽያጭ መረጃ ለማደራጀት እና መረጃውን አግባብ ባለው አስፈጻሚ አካል በተጠየቀ ጊዜ ለመስጠት የተስማማ፤

፲/ የአቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪው የሚዘጋጅ ቡና ግዥ ሆነ ሽያጭ በህጋዊ ግብይት ብቻ መከናወኑን ሙሉ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ አውቆ የተስማማ፤ እና

፲፩/ በቡና ንግድ በወንጀል ወይም በአስተዳደር ቅጣት ተወስኖበት ከነበረ ቅጣቱን የፈጸመ ወይም የወንጀል ቅጣቱ የተገደበለት ከሆነ ገደቡን የፈጸመ፤

መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

## ፳፫. የቡና ገለባ አቀነባባሪነት የብቃት ማረጋገጫ

ማንኛውም ሰው የቡና ገለባ አቀነባባሪነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው፡-

፩/ በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ሲሆን የሥራ አድራሻ ያለው፤ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ ቋሚ ንብረት እና የመኖሪያ አድራሻ ያለው፤

፪/ በማንኛውም ንግድ ወይም በማህበራዊ አገልግሎት ወይም በተሠማራበት የሙያ መስክ መልካም አፈጻጸምና ስም ያለው ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማምጣት የሚችል፤

፫/ በባለስልጣኑ የተዘጋጀውን የቴክኒክ መስፈርት ያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይም አግባብ ባለው አካል በጸደቀ የኪራይ ውል ያገኘው የቡና ገለባ ማቀነባበሪያና ማከማቻ ያለው፤

፬/ በሚመለከተው መንግሥታዊ አካል የተረጋገጠ ስለማዘጋጃ ኢንዱስትሪ የሥራ እንቅስቃሴ የአከባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ ማቅረብ የሚችል፤ እና

፭/ ከቡና ገለባ አዘገጃጀትና ጥራት አያያዝ ጋር በተያያዘ ዕውቀትና ክህሎት ያለው ቋሚ ባለሙያ የቀጠረ፤

መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

9/ Organizes coffee purchase, process, sells and stock information and agrees to provide for relevant executing organ upon request;

10/ Agrees to take full responsibility about the legality of the transaction to be processed in his supply coffee processing; and warehousing industry; and

11/ if criminally or administratively convicted in coffee trade, Completes the punishment; if criminal punishment is Suspended, completes the suspension;

## 23. Coffee husk processor's Certificate of Competence

The coffee husk processor's Certificate of Competence shall be issued, when any person:

1/ Has a business address for a juridical person; has fixed asset and residence address for a natural person;

2/ Provides evidence from the concerned organ about good performance and reputation of any business work or social service or professional engagement;

3/ Owns or has leased through approved contract by Authorized organ a coffee husk processing and warehousing which meets technical standards issued by the Authority;

4/ Provides environmental impact assessment document from relevant government organ about export coffee processing and warehousing industries; and

5/ Employs permanently professional with knowledge and skill about coffee husk processing and quality management.

https://chilot.me



**፳፬. የቡና ቅጠል አቀነባባሪነት የብቃት ማረጋገጫ**

ማንኛውም ሰው የቡና ቅጠል አቀነባባሪነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው:-

፩/ በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ሲሆን የሥራ አድራሻ ያለው፤ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ ቋሚ ንብረት እና የመኖሪያ አድራሻ ያለው፤

፪/ በማንኛውም ንግድ ወይም በማህበራዊ አገልግሎት ወይም በተሠማራበት የሙያ መስክ መልካም አፈጻጸምና ስም ያለው ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማምጣት የሚችል፤

፫/ በባለቤትነት የያዘው ወይም አግባብ ባለው አካል በጸደቀ የኪራይ ውል ያገኘው የቴክኒክ መስፈርት ያሟላ የቡና ቅጠል ማቀነባበሪያና ማከማቻ ያለው፤

፬/ በሚመለከተው መንግሥታዊ አካል የተረጋገጠ ስለማዘጋጀ ኢንዱስትሪ የሥራ እንቅስቃሴ የአከባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ ማቅረብ የሚችል፤ እና

፭/ ከቡና ቅጠል አዘገጃጀትና ጥራት አያያዝ ጋር በተያያዘ ዕውቀትና ክህሎት ያለው ቋሚ ባለሙያ የቀጠረ፤

መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

**፳፭. የጥብቅ የወጪ ቡና ማከማቸት አገልግሎት ሰጪነት የብቃት ማረጋገጫ**

ማንኛውም ሰው የጥብቅ የወጪ ቡና ማከማቸት አገልግሎት ሰጪነት የብቃት ማረጋጋጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው:-

፩/ በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ሲሆን የሥራ አድራሻ ያለው፤ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ ቋሚ ንብረት እና የመኖሪያ አድራሻ ያለው፤

፪/ በማንኛውም ንግድ ወይም በማህበራዊ አገልግሎት ወይም በተሠማራበት የሙያ መስክ መልካም አፈጻጸምና ስም ያለው ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማምጣት የሚችል፤

**24. Coffee leaf processor's Certificate of Competence**

The coffee leaf processor's Certificate of Competence shall be issued, when any person:

1/ Has a business address for a juridical person; has fixed asset and residence address for a natural person;

2/ Provides evidence from relevant organ about good performance and reputation of any business work or social service or professional engagement;

3/ Owns or has leased through approved contract by Authorized organ a coffee leaf processing and warehousing which meets technical standards issued by the Authority;

4/ Provides environmental impact assessment document from relevant government organ about export coffee processing and warehousing industries; and

5/ Employs permanently professionals with knowledge and skill about coffee leaf processing and quality management.

**25. Bonded export coffee warehouse service provider's Certificate of competence**

The Bonded export coffee warehouse service provider's Certificate of Competence shall be issued, when any person:

1/ Has a business address for a juridical person; has fixed asset and residence address for a natural person;

2/ Provides evidence from relevant organ about good performance and reputation of any business work or social service or professional engagement;

https://chilot.me



፫/ በባለስልጣኑ የተዘጋጀውን የቴክኒክ መስፈርት ያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይም ስልጣን ባለው አካል በጸደቀ የኪራይ ውል ያገኘው ጥብቅ የወጪ ገቢያ ቡና ማከማቻ ያለው፤

፬/ የተለያየ ባህሪ ወይም ደረጃ ያላቸውን የቡና ዓይነቶች ለይቶ ለማከማቸት የሚያስችለው አሠራር ያለው፤

፭/ በህግ የሀገሪቱን የወጪ ቡና የጥራት ደረጃ ለማስጠበቅ የተቀመጡ ግዴታዎችንና መስፈርቶችን ጠብቆና ብሔራዊ ጥቅምን ከሚጎዳ ተግባር ተቆጥቦ ለመሥራት የተስማማ፤

፮/ ስለቡና ግዥ፣ ክምችትና ጭነት መረጃ ለማደራጀት እና መረጃውን አግባብ ባለው አስፈጻሚ አካል በተጠየቀ ጊዜ ለመስጠት የተስማማ፤

፯/ በጥብቅ የወጪ ቡና ማከማቻ መጋዘኑ ስለሚከማች ቡና እና የጭነት እንቅስቃሴ በህጋዊ መንገድ ብቻ መከናወኑን አስመልክቶ ሙሉ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ አውቆ የተስማማ፤ እና

፰/ በቡና ንግድ በወንጀል ወይም በአስተዳደር ቅጣት ተወስኖበት ከነበረ ቅጣቱን የፈጸመ ወይም የወንጀል ቅጣቱ የተገደበለት ከሆነ ገደቡን የፈጸመ፤

መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

**፳፮. <u>የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ጅምላ ነጋዴነት የብቃት ማረጋገጫ</u>**

ማንኛውም ሰው የሀገር ውስጥ ፍጆታ የቡና ጅምላ ነጋዴነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው:-

፩/ በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ሲሆን የሥራ አድራሻ ያለው፤ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ ቋሚ ንብረት እና የመኖሪያ አድራሻ ያለው፤

3/ Own or has leased through approved contract by Authorized organ a bonded export coffee warehousing which meets technical standards issued by the Authority;

4/ Has operational procedures to store by identifying different characteristics and grades of coffee types;

5/ Agrees to work with the national export coffee quality standard set by a law and restrains from harming national interest;

6/ Organizes coffee purchase, store and loading information and agrees to provide for relevant executing organ upon request;

7/ Agrees to take full responsibility about the legality of the transaction to be stored and loading activity in his bonded export coffee warehousing; and

8/ if criminally or administratively convicted in coffee trade, completes the punishment; if criminal punishment is Suspended, completes the suspension.

**26. <u>domestic consumption Coffee wholesaler's Certificate of Competence</u>**

The domestic consumption wholesaler's Certificate of Competence shall be issued, when any person:

1/ Has a business address for a juridical person; has fixed asset and residence address for a natural person;

https://chilot.me



፪/ በማንኛውም ንግድ ወይም በማህበራዊ አገልግሎት ወይም በተሠማራበት የሙያ መስክ መልካም አፈጻጸምና ስም ያለው ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማምጣት የሚችል፤

፫/ አግባብ ባለው የክልል አካል የተዘጋጀውን የቴክኒክ መስፈርት ያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይም አግባብ ባለው አካል በጸደቀ የኪራይ ውል ያገኘው የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ማከማቻ መጋዘን ያለው፤

፬/ ቡናን ለማከፋፈል ንግድ ፈቃድ በሚጠይቅበት ዞን፣ ከተማ ወይም ወረዳ የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና አከፋፋይ ስላለመኖሩ ወይም በቂ ስላለመሆኑ ከሚመለከተው የመንግሥት አካል ማረጋገጫ ሰነድ የሚያቀርብ፤

፭/ የሀገሪቱን የቡና ጥራት መስፈርት አክብሮ ቡና ለመያዝና ለማከፋፈል የተስማማ፣

፮/ ስለቡና ግዥ፣ ክምችትና ሽያጭ መረጃ ለማደራጀት እና መረጃውን አግባብ ባለው አስፈጻሚ አካል በተጠየቀ ጊዜ ለመስጠት የተስማማ፤ እና

፯/ በቡና ንግድ በወንጀል ወይም በአስተዳደር ቅጣት ተወስኖበት ከነበረ ቅጣቱን የፈጸመ ወይም የወንጀል ቅጣቱ የተገደበለት ከሆነ ገደቡን የፈጸመ፤ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

## ፳፯. የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ችርቻሮ ነጋዴነት የብቃት ማረጋገጫ

ማንኛውም ሰው የሀገር ውስጥ የቡና ፍጆታ የቡና ችርቻሮ ነጋዴነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው:-

2/ Provides evidence from relevant organ about good performance and reputation of any business work or social service or professional engagement;

3/ Owns or has leased through approved contract by Authorized organ a domestic consumption coffee warehousing which meets technical standards issued by the appropriate regional organ;

4/ Provides document from relevant government organ about none existence or insufficiency of domestic consumption coffee wholesaler in zone, city or Woreda, where he applied for coffee wholesaler trade license;

5/ Agrees to manage and distribute coffee as per the national coffee quality standards,

6/ Organizes coffee purchase, store and sells information and agrees to provide for relevant executing organ upon request; and

7/ if criminally or administratively convicted in coffee trade, Completes the punishment; if criminal punishment is Suspended, completes the suspension.

## 27. Domestic Consumption Coffee retail Trader's certificate of Competence

The domestic consumption retail trader's Certificate of Competence shall be issued, when any person:

https://chilot.me



፩/ በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ሲሆን የሥራ አድራሻ ያለው፣ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ ቋሚ ንብረት እና የመኖሪያ አድራሻ ያለው፣

፪/ በባለቤትነት የያዘው ወይም አግባብ ባለው አካል በጸደቀ የኪራይ ውል ያገኘው የንግድ መደብር ያለውና መደብሩ ለቡና ማስቀመጫ የተለየ ስፍራ ያለው፣

፫/ የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ለመያዝና ለመቸርቸር ህጋዊ ሥርዓት ጠብቆ ለመሥራት የተስማማ፣ እና

፬/ ስለቡና ግዥ፣ ክምችት ሽያጭ መረጃ ለማደራጀት እና መረጃውን አግባብ ባለው አስፈጻሚ አካል በተፈለገ ጊዜ ሲጠየቅ ለመስጠት የተስማማ፣

መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

1/ Has a business address for a juridical person; has fixed asset and residence address for a natural person;

2/ Owns or has leased through approved contract by relevant authorized organ trade store and special place for coffee storage in the store;

3/ Agrees to legally handle and retail domestic consumption coffee; and

4/ Organizes coffee purchase, store and sells information and agrees to provide for relevant executing organ upon request.

## ፳፰. የቡና የንግድ ሥራ ወኪልነት የብቃት ማረጋገጫ

ማንኛውም ሰው የቡና ንግድ ሥራ ወኪልነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው:-

፩/ በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ሲሆን የሥራ አድራሻ ያለው፣ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ ቋሚ ንብረት እና የመኖሪያ አድራሻ ያለው፣

፪/ በማንኛውም ንግድ ወይም በማህበራዊ አገልግሎት ወይም በተሠማራበት የሙያ መስክ መልካም አፈጻጸምና ስም ያለው ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማምጣት የሚችል፣

፫/ በዘርፉ ዕውቀትና ክህሎት ያለው ስለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣

፬/ ስለቡና ግዥ፣ ክምችት፣ ሽያጭና ጭነት መረጃ ለማደራጀት እና መረጃውን አግባብ ባለው አስፈጻሚ አካል በተጠየቀ ጊዜ ለመስጠት የተስማማ፣ እና

፭/ በቡና ንግድ በተያያዘ በወንጀል ወይም በአስተዳደር ቅጣት ተወስኖበት ከነበረ ቅጣቱን የፈጸመ ወይም የወንጀል ቅጣቱ የተገደበለት ከሆነ ገደቡን የፈጸመ፣

መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

## 28. Coffee trade agent's certificate of competence

The coffee trade agent's Certificate of Competence shall be issued, when any person:

1/ Has a business address for a juridical person; has fixed asset and residence address for a natural person;

2/ Provides evidence from relevant organ about good performance and reputation of any business work or social service or professional engagement;

3/ Provides evidence for having experience and knowledge of the sector;

4/ Organizes coffee purchase, store, sells and loading information and agrees to provide for relevant executing organ upon request; and

5/ If criminally or administratively convicted in coffee trade, Completes the punishment; if criminal punishment is Suspended, completes the suspension;

https://chilot.me



**፳፱. ቡና የማጓጓዝ አገልግሎት ሰጪነት የብቃት ማረጋገጫ**

ማንኛውም ሰው ቡና የማጓጓዝ አገልግሎት ሰጪነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው:-

፩/ በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ሲሆን የሥራ አድራሻ ያለው፣ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ ቋሚ ንብረት እና የመኖሪያ አድራሻ ያለው፣

፪/ ከሚመለከተው የመንግሥት አካል የጭነት ትራንስፖርት ንግድ ፈቃድ የሚያቀርብ፣

፫/ ባለስልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል ከሚመለከተው ትራንስፖርት ተቆጣጣሪ አካል ጋር በመሆን የሚያወጣውን የቡና ማጓጓዝ ወይም የጭነት የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይም አግባብ ባለው አካል በጸደቀ የኪራይ ውል የተገኘው የጭነት ተሽከርካሪ ያለው፣

፬/ ቡና ሲያጓጉዝ የሚደርሰውን አደጋ ለመካስ የሚያስችል የመድህን ዋስትና ያለው ስለመሆኑ ማስረጃ የሚያቀርብ፣ እና

፭/ ስለሚያጓጉዘው ወይም ስለሚጭነው ቡና ህጋዊነት የማረጋገጥ ሙሉ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ አውቆ የተስማማ፣

መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

**፴. ቡና የመጫንና የማራገፍ አገልግሎት ሰጪነት የብቃት ማረጋገጫ**

ማንኛውም ሰው ቡና በመጫንና በማራገፍ አገልግሎት ሰጪነት ለመሰማራት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው:-

፩/ በዘመኑ የታደሰ የቀበሌ የነዋሪነት መታወቂያ የሚያቀርብ፣

፪/ ከአከባቢው አስተዳደር የመጫንና የማራገፍ አገልግሎት ለመስጠት በማህበር ተደራጅቶ ፈቃድ ያለው ወይም በግል ለመሰማራት የሚያስችል ማስረጃ የሚያቀርብ፣ እና

**29. Coffee Transport Service Provider's Certificate of Competence**

The coffee transport service providers Certificate of Competence shall be issued, when any person:

1/ Has a business address for a juridical person; has fixed asset and residence address for a natural person;

2/ Provides loading Transport Trade license from relevant government organ;

3/ Owns or has rented through approved contract by authorized organ loading truck, which meets coffee transport and loading technical requirement issued by the Authority or appropriate regional organ in collaboration with relevant Transport regulatory organ;

4/ Provides evidence for having insurance to compensate the risk of transporting coffee; and

5/ Agrees to take full responsibility about the legality of coffee he is transporting and loading.

**30. Coffee loading and unloading service provider's certificate of competence**

The coffee loading and unloading service provider's Certificate of Competence shall be issued, when any person:

1/ Provides renewed Kebele's residential ID card;

2/ Provides evidence from local administration about forming association or private engagement for loading and unloading service delivery; and

https://chilot.me



፫/ ስለሚጫነው ወይም ሰለሚያራግፈው ቡና ህጋዊነት የማረጋገጥ ሙሉ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ አውቆ የተስማማ፤

መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

**፴፩. <u>የቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ አገልግሎት ሰጪነት የብቃት ማረጋገጫ</u>**

ማንኛውም ሰው የቡና ጥራት ምርመራ እና ደረጃ ምደባ ላቦራቶሪ አግልግሎት ሰጪነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው:-

፩/ በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ሲሆን የሥራ አድራሻ ያለው፤ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ ቋሚ ንብረት እና የመኖሪያ አድራሻ ያለው፤

፪/ የባለሥልጣኑን አሠራርና የአደረጃጀት የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ የቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ላቦራቶሪ ያለው፤

፫/ በቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ ልዩ ስልጠና የወሰደ ባለሙያ በቋሚነት የቀጠረ፤

፬/ ስለቡና ጥራት፣ ደረጃና መጠን በእያንዳንዱ የቡና ዓይነት ከነባለቤቱ መረጃ ለማደራጀት እና መረጃውን አግባብ ባለው አስፈጻሚ አካል በተጠየቀ ጊዜ ለመስጠት የተስማማ፤

፭/ በህግ የሀገሪቱን የቡና ጥራት ደረጃ ለማስጠበቅ የተቀመጡ ግዴታዎችንና መስፈርቶችን ጠብቆ ብሄራዊ ጥቅምን ከሚጎዳ ተግባር ተቆጥቦ ለመሥራት የተስማማ፤ እና

፮/ በቡና ንግድ በወንጀል ወይም በአስተዳደር ቅጣት ተወስኖበት ከነበረ ቅጣቱን የፈጸመ ወይም የወንጀል ቅጣቱ የተገደበለት ከሆነ ገደቡን የፈጸመ፤

መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

3/ Agrees to take full responsibility about athe legality of coffee loading; and unloading activities.

**31. <u>Coffee quality inspection and grading service provider’s certificate of competence</u>**

The Coffee quality inspection and grading service provider’s Certificate of Competence shall be issued, when any person:

1/ Has a business address for a juridical person; has fixed asset and residence address for a natural person;

2/ Owns a coffee quality inspection and grading center which fulfills organizational and operational technical standards of the Authority;

3/ Employs permanently a professional with special training on coffee quality inspection and grading;

4/ Organizes coffee quality, grade and quantity information for each coffee type including the owner and agrees to provide for relevant executing organ upon request;

5/ Agrees to work with the national export coffee quality standards set by a law and restrains from harming national interest; and

6/ if criminally or administratively convicted in coffee trade, Completes the punishment; if criminal punishment is Suspended, completes the suspension;

https://chilot.me



## ንዑስ ክፍል ሁለት

### የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥና አስተዳደር

**፴፪. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ**

፩/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው:-

ሀ) በወጪ ቡና ማዘጋጀትና ማከማቸት፣ ቡና ላኪነት፣ የወጪ ቡና ቆዪነት፣ የጥብቅ ቡና ማከማቸት፣ በወጪ ቡና ንግድ ሥራ ወኪልነት፣ በጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ አገልግሎት ሰጪነት ሥራ የሚሰማራ ከሆነ ማመልከቻውን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

ለ) የቡና አቅራቢነት፣ የሀገር ውስጥ ቡና ቆዪነት፣ በአቅርቦት ቡና ማዘጋጀትና ማከማቸት፣ በቡና ገለባ አቀነባባሪነት፣ በቡና ቅጠል አቀነባባሪነት፣ በሀገር ውስጥ ቡና ፍጆታ ጅምላ ነጋዴነት፣ በሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ችርቻሪ ነጋዴነት፣ በሀገር ውስጥ ቡና ንግድ ወኪልነት፣ የቡና ማጓጓዝ አገልግሎት ሰጪነት፣ የቡና መጫንና ማራገፍ አገልግሎት ሰጪነት ከሆነ፣ ማመልከቻውን አግባብ ላለው የክልል አካል ማቅረብ አለበት፡፡

ሐ) ከማመልከቻው ጋር የተጠየቀውን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት በዚህ ደንብ የተደነገጉት መስፈርቶች መሟላታቸውን የሚያሳዩ ማስረጃዎችንና ባለስልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የሚጠየቁ ሌሎች መረጃዎችን አሟልቶ ማቅረብ አለበት፡፡

## Sub-section two

### Issuance and administration of Certificate of Competence

**32. Application for Certificate of Competence**

1/ Any Person who wants to obtain the certificate of competence should:

a) submit application to the Authority, if he wants to engage in export coffee processing and warehousing service, coffee exporting, export coffee roasting or roasting and grinding, bonded warehousing service, export trading agent, coffee quality inspecting and grading service or any other activities related with these.

b) submit application to the appropriate regional organ, if he wants to engage in coffee supplying, domestic coffee consumption roasting, supply coffee processing and warehousing, coffee husk processing, coffee leaf processing, domestic coffee consumption wholesaling, domestic consumption retailing trade, domestic consumption trading agent, coffee transporting service, coffee loading and unloading service and other related activities with these.

c) Provide with the application, evidences for fulfilling the requirements provided by this Regulation and provide other information according to directive to be issued by the Authority or the appropriate regional organ to obtain the requested certificate of competence.

https://chilot.me



፪/ ባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል ማመልከቻው ከቀረበለት ቀን ጀምሮ በ፲፭ የሥራ ቀናት ውስጥ አጣርቶ የብቃት ማረጋገጫ መስጠት ወይም የማይጋባው መሆኑ የሚገልፅ ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል፤

፫/ ባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል አመልካቹ የብቃት ማረጋገጫው የማይገባው መሆኑን በወሰነ ጊዜ የክልከላውን ምክንያት በውሳኔው ላይ በዝርዝር በማስቀመጥ ለአመልካቹ በጽሁፍ መስጠት ይኖርበታል፤

፬/ ባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ አመልካች ውሳኔው በተሰጠው በ፴ የሥራ ቀናት ውስጥ ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

**፴፫. የብቃት ማረጋገጫ ስለማሳደስ**

፩/ በዚህ ደንብ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም ሰው በሚቀመጥ የጊዜ ገደብ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን በየአመቱ ማሳደስ ይኖርበታል፡፡

፪/ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ያላሳደሰ እንደሆነ ይህን ደንብ ተከትሎ በሚወሰን መመሪያ በሚወሰን ተጨማሪ ጊዜ እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ በሚወሰን የቅጣት መጠን በገንዘብ ቅጣት ማሳደስ ይችላል፡፡

**፴፬. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለማገድ እና መሰረዝ**

፩/ በዚህ ደንብ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) የምስክር ወረቀቱ የተሰጠባቸውን መስፈርቶች አጓድሎ ሲገኝ፣

2/ The Authority or the appropriate regional organ shall decide on the application within 15 working days from the date of receipt of the application;

3/ When the Authority or the appropriate regional organ rejects the application for certificate of competence, it shall provide a letter for the applicant stating the detailed reasons in written form;

4/ Any applicant who is dissatisfied with the decision of the Authority or the appropriate regional organ may appeal to appropriate court within 30 working days from the date of receipt of the decision.

**33. Renewal of certificate of competence**

1/ Any person who received certificate of competence shall renew the certificate of competence annually within the specified time.

2/ If certificate of competence is not renewed during the specified time limit, it may be renewed in extra time with fine penalty decided by the regulation of the council of ministers.

**34. Suspension and Revocation of Certificate of Competence**

**1/** Where a person issued with a certificate of competence in accordance with this Regulation fails to:

a) maintain the conditions upon the basis of which the certificate of competence has been issued,

https://chilot.me



ለ) በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ያላሳደሰ እንደሆነ፣ ወይም

ሐ) የአዋጁን ወይም የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ወይም አዋጁንና ይህን ደንብ ለማስፈጸም የወጡ መመሪዎችን ተላልፎ ሲገኝ፤

ባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል ጉድለቱን እንዲያስተካክል በማዘዝ የምስክር ወረቀቱን አግዶ ሊያቆየው ይችላል፤ መታገዱንም ለሚመለከታቸው አካላት በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

፪/ በዚህ ደንብ መሠረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የያዘ ሰው፦

ሀ) የምስክር ወረቀቱን ያገኘው ሀሰተኛ ማስረጃ በማቅረብ ሆኖ ከተገኘ፣

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለምስክር ወረቀቱ መታገድ ምክንያት የሆነውን ጉድለት በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማስተካከል ካልቻለ፣ ወይም

ሐ) በአዋጁ አንቀጽ ፲፱ የተደነገገውን በመተላለፍ በወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ ከተፈረደበት፤

የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ በባሥልጣኑ ወይም አግባብነት ባለው የክልል አካል ይሰረዛል፡፡

፫/ በባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ሰው ቅሬታ ካለው ውሳኔው ከደረሰው ቀን ጀምሮ ባሉት ፷ የሥራ ቀናት ውስጥ ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

b) renew the certificate of competence within time limit, or

c) Obey the provisions of the proclamation or this Regulation or directives;

the Authority or the appropriate regional organ by orders to rectify the failures may suspend the certificate of competence and inform relevant organ in written form.

2/ Where the holder of a certificate of competence issued in accordance with this Regulation:

a) found to have obtained the certificate of competence upon presentation of false evidence,

b) fails to rectify the irregularities which caused the suspension of the certificate of competence pursuant to sub-article (1) of this Article within the specified time limit, or

c) has committed a criminal offense in violation of Article 19 of the proclamation;

the Authority or the appropriate regional organ may revoke the certificate of competence.

3/ A person whose certificate of competence is suspended or revoked by the Authority or appropriate regional organ may appeal to appropriate court within 60 working days from the date of receipt of the decision.

https://chilot.me



**፴፭. የእግድ ወይም የመሠረዝ ውጤት**

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፬ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ሰው በዕገዳው ወይም በመሰረዙ ላይ የቀረበው ይግባኝ በመታየት ላይ እያለ በቡና ግብይት ወይም በአገልግሎት ሰጪነት ላይ ሊሠማራ አይችልም፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ሰው በዚህ ደንብ የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟሉ መገልገያዎቹን፣ መሳሪያዎቹንና ዕቃዎቹን የጸና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው ሌላ ሰው እንዲጠቀምባቸው ሊፈቅድ ይችላል፡፡

**ክፍል አምስት**

**የቡና ጥራት እና ግብይት ቁጥጥር አሠራር**

**፴፮. የቡና ጥራት ቁጥጥር አሠራር**

፩/ ቡና ሲለቀም፣ ሲዘጋጅ፣ ሲከማች፣ ሲጓጓዝ ተፈጥሯዊ ጥራት ተጠብቆ ለገበያ እንዲቀርብ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቀይ እሸት እና ጀንፈል ቡና ወደ ግብይት ማዕከላት ሲቀርብ የቀይ እሸት ወይም የጀንፈል ቡና ጥራት ደረጃ መሠረት ስለመቅረቡ ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

፫/ የቀይ እሸት ቡና በተለቀመበት ዕለት ወደ የታጠበ የአቀርቦት ቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ገብቶ በጥራት ስለመዘጋጀቱ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

**35. Consequences of Suspension or Revocation**

1/ A person whose certificate of competence has been suspended or revoked pursuant to Article 34 of this Regulation shall not engage in coffee transaction irrespective of the fact that his appeal against the suspension or revocation is under consideration.

2/ Notwithstanding sub-article (1) of this Article, a person whose certificate of competence has been suspended or revoked may authorize the use of his facilities, machineries and equipment by another person who fulfills the requirements of this regulation holding a valid certificate of competence.

**SECTION FIVE**

**COFFEE QUALITY AND TRANSACTION INSPECTION PROCESS**

**36. Coffee Quality Inspection Process**

1/ Monitoring and inspection shall be made during Coffee picking, processing, storing, drying and transporting to preserve the natural quality.

2/ Without prejudice the provisions of sub-Article (1) of this article, when red cherry coffee and coffee with pulp is supplied to transaction center, it shall be inspected that it is supplied according to red cherry coffee and coffee with pulp quality standard.

3/ Red cherry coffee shall be Monitored and inspected that it is processed with quality after entering to washed supply coffee industry on the picked date.

https://chilot.me



፬/ ጀንፈል ቡና በተዘጋጀው የአደራረቅ የቴክኒክ መስፈርት መሠረት ስለመዘጋጀቱና ስለ መከማቸቱ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

፭/ የአቅርቦት ቡና ወደ ወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ገብቶ በጥራት ስለመዘጋጀቱና ስለመከማቸቱ፣ በቃጫ ጆንያ ወይም በሌላ በባለሥልጣኑ በተፈቀደ መያዣ ታሽጎ ስለመያዙ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

፮/ የአቅርቦት ቡና ከተመረተበት አካባቢ ታሽጎ ከመሸኘቱ በፊት ለባለቤቱ የሚመለስ ወካይ ናሙና ተወስዶ የጥሬ ቡና ምርመራ ይደረጋል፡፡

፯/ የአቅርቦት ቡና ለወጪ ገበያ ወይም ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ወደ ገበያ ከመቅረቡ በፊት በወጣው የቡና ጥራትና ጣዕም ምርመራ የቴክኒክ መስፈርት መሠረት ወካይ ናሙና ተወስዶ የጥራት ደረጃው እንዲመደብ ይደረጋል፡፡

፰/ የተቆላ ወይም ተቆልቶ የተፈጨ ቡና ወይም በሌላ መልኩ እሴት የተጨመረበት ቡና በተቀመጠው የቴክኒክ መስፈርት መሠረት በጥራት ስለመቀነባበሩ፣ በሚፈለገው ደረጃ ስለመታሸጉና ስለመከማቸቱ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

፱/ በማንኛውም መልኩ ቡና የሚጫንበት የጭነት ተሽከርካሪ ወይም ኮንቴነር ቡናን ለመጫን አስፈላጊውን የጥራት ደረጃ ስለማሟላቱ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

**፴፯. <u>የቡና ግብይት ቁጥጥር</u>**

፩/ በማንኛውም የቡና አምራች የቀይ እሸት ቡና ለታጠበ ቡና ዝግጅት የሚቀርብ ከሆነ ከተለቀመበት ጊዜ ጀምሮ ከስምንት ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ወደ የመጀመሪያ ደረጃ ቡና ግብይት ማዕከላት ስለመግባቱ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

4/ Coffee with pulp shall be Monitored and inspected that it is processed and stored according to drying technical criteria set.

5/ Supplied coffee shall be monitored and inspected that it is processed and stored with quality, packed in jute bags or any other packaging material approved by the Authority after entering export coffee processing and warehousing industry.

6/ Raw Coffee inspection shall be undertaken before supply coffee dispatched from coffee growing area by taking representative sample to be returned back to the owner.

7/ Supply coffee, before export market or domestic consumption, shall be graded by taking representative sample based on coffee quality inspection and grading technical standards set.

8/ Roasted or roasted and grinded or prepared in other value added from coffee, shall be monitored and inspected that it is processed with quality, packed by standard packaging and stored according to the technical requirements set.

9/ Any form of coffee loading truck or container shall be monitored and inspected that it fulfills appropriate quality standards.

**37. <u>Inspection of Coffee transaction process</u>**

1/ When red cherry coffee is supplied by any coffee producer for washed coffee process, shall be monitored and inspected that it is entered first level transaction center within eight hours starting from harvested time.

https://chilot.me



፪/ በማንኛውም የቡና አምራች የሚዘጋጅ የጀንፈል ቡና ባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል በሚያወጣው የቴክኒክ መስፈርት መሠረት ጥራቱን በጠበቀ ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ እንዲከማች እና ስለመከማቸቱ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀት (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቡና አምራች አርሶ አደር ጀንፈል ቡና ከአንድ የምርት ዘመን በላይ እንዳይከማች ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

፬/ ማንኛውም የታጠበ የአቅርቦት ቡና በምርት ዘመኑ እስከ ነሐሴ ፴ ቀን ድረስ ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በአማራጭ ግብይት ውል መሠረት ለቡና ላኪው ስለመቅረቡ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

፭/ ማንኛውም ያልታጠበ የአቅርቦት ቡና በምርት ዘመኑ እስከ ጥቅምት ፴ ቀን ድረስ ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በአማራጭ ግብይት ውል መሠረት ለቡና ላኪው ስለመቅረቡ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

፮/ ማንኛውም ቡና አዘጋጅቶ ለወጪ ገበያ የሚያቀርብ ሰው ለወጪ ገበያ ያዘጋጀውን የታጠበ ቡና የምርት ዘመኑ ማጠናቀቂያ ጊዜ እስከሆነው ጥቅምት ፴ ቀን ድረስ በወጪ ገበያ ስለመሸጡ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

፯/ ማንኛውም ቡና አዘጋጅቶ ለወጪ ገበያ የሚያቀርብ ሰው ለወጪ ገበያ ያዘጋጀውን ያልታጠበ ቡና የምርት ዘመኑ ማጠናቀቂያ ጊዜ እስከሆነው ጥር ፴ ቀን ድረስ ስለመሸጡ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

፰/ በባለስልጣኑ የተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ያለበቂ ምክንያት ማለፉን ሲያረጋግጥ የጊዜ ገደቡ ከተጠናቀቀ በኋላ ባለው አንድ ወር ውስጥ የቡናውን ጠቅላላ ዋጋ ሁለት በመቶ ቅጣት ለመንግሥት ገቢ ከተፈጸመ እንዲሁም የጊዜ

2/ Coffee with pulp prepared by any coffee producer shall be monitored and inspected that it is stored in quality coffee processing warehousing industry according to technical standard set by Authority or appropriate regional organ.

3/ Without prejudice to sub article (2) of this article, coffee producer shall be monitored and inspected for not storing coffee with pulp more than one coffee production year.

4/ Any washed supply coffee shall be monitored and inspected that it is supplied to Ethiopian Commodity exchange or to the coffee exporter through alternative transaction contract until September 5 (Nehassie 30) in its production season.

5/ Any unwashed supply coffee shall be monitored and inspected that it is supplied to Ethiopian Commodity exchange or to the coffee exporter through Alternative transaction contract until November 9 (Tikimit 30) in its production season.

6/ Any person, who processed washed coffee for export market, shall be monitored and inspected that he sells until November 9 (Tikimit 30), the end of coffee production season.

7/ Any person, who processed unwashed coffee for export market, shall be monitored and inspected that he sells until February 7 (Tir 30) ,the end of coffee production season.

8/ When the Authority confirms that the time limit is not met with sufficient ground, may allow the sell, two percent of total coffee value during the first month and 5%(five percent) of total coffee value as a fine for

https://chilot.me



ገደቡ ከተጠናቀቀ በኋላ ባለው በሁለተኛ ወር ውስጥ የቡናውን ጠቅላላ ዋጋ ፭ በመቶ(አምስት በመቶ) ቅጣት ለመንግሥት ገቢ ከተፈጸመ በኋላ እንዲሸጥ ይፈቀዳል፡፡

፱/ በአቅርቦትና በወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ የሚኖረውን የቡና ክምችት እንደአግባብነቱ በባለስልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል በሚወጣው መርሐ ግብር መሠረት በዓመት አንድ ጊዜ የቡና ክምችት ቆጠራ ይደረጋል፡፡

፲/ የቡና ክምችት ቆጠራ ተደርጎ በቡና ግብይት ሂደት በቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪው ሊኖር የሚገባው የቡና ክምችት መጠን ተሰልቶ በማነስም ሆነ በመብለጥ በሚለየው የቡና ክምችት ላይ እንደአግባብነቱ በባለስልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ሕጋዊና አስተዳዳራዊ እርምጃ እንዲወሰድ ይደረጋል፡፡

፲፩/ ማናቸውም የአቅርቦትና የወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ከተገልጋዩ ጋር በገባው ውል መሠረት ላዘጋጀው ቡና በኢንዱስትሪው ስለመዘጋጀቱ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለመሰጠቱ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

፲፪/ ቡናው የተመረተበት አካባቢ ወይም የአቅርቦት ቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ወይም የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም የወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ወይም የሀገር ውስጥ ቡና ሸማች አካባቢ በአግባቡ ስለመሸኘቱና ስለመድረሱ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፤ ማንኛውም ሰው ማጓጓዝ የሚችለው የግል ፍጆታ የቡና መጠን ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

the government during the second month after the expiry of the time limit.

9/ Coffee stock available in supply and export coffee processing and warehousing industries, shall be counted once in a year in accordance with the schedule issued by the Authority or appropriate regional organ.

10/ Legal and administrative measures shall be taken on negative and positive coffee stock balance on coffee processing and warehousing industry identified during coffee transaction process based on directives issued by the Authority or appropriate regional organ.

11/ Any supply and export coffee processing and warehousing industry, shall be monitored and inspected that it provides certificate for processed coffee, verifying the processing of it at its industry in accordance with contract entered with client.

12/ Coffee shall be monitored and inspected that it is properly dispatched and arrived at coffee growing area or supply coffee processing industry or Ethiopian Commodity Exchange or export processing and warehousing industry or domestic coffee consuming area; private use coffee amount that can be transported by any person, shall decided by directive issued by the Authority.

https://chilot.me



፲፫/ የወጪ ገበያ ቡና አስፈላጊውን መስፈርት አሟልቶ ከተሸኘ በኋላ ከሀገር ስለመውጣቱ በሀገሪቱ ህጋዊ መውጫ በሮች ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

፴፰. <u>የተከለከሉ አሰራሮች</u>

በአዋጁ የተከለከሉ ተግባራትና አሠራሮች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ቡና አምራች ወይም አዘጋጅ ወይም የግብይት ተሳታፊ በቡና ልማት፣ ለቀማ፣ ዝግጅት፣ ግብይት፣ ማከማቸት እና ማጓጓዝ ሂደት ላይ:-

፩/ አረንጓዴ ቡና መልቀም፣ ቡናን መሸምጠጥ ወይም የተለያየ ብስለት ደረጃ ያለው ቡና መቀላቀል፤

፪/ ቡናን ክብደቱ እንዲጨምር በአፈር ማሸት፣ ከባዕድ አካላት ጋር ማደባለቅ ወይም በውሃ መዘፍዘፍ፤

፫/ ቡናን በመንገድ ወይም በመሬት ላይ መጨፍለቅ ወይም ለማድረቅ ማስጣት ወይም መርቡሽ ቡና ማዘጋጀት ወይም በማንኛውም ሁኔታ የቡናውን ጣዕምና ጥራት ከሚያበላሽ ባዕድ ነገር እንዲነካካ ማድረግ፤

፬/ ለቡና ተክሉ አገልገሎቱን ያላጠናቀቀ ቅጠል ሸምጥጦ ለገበያ ማቅረብ፤

፭/ ባለስልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል አገልግሎት ላይ እንዲውል ከሚፈቅደው የቃጫ ጆንያ ወይም ሌላ የቡና መያዣ ውጪ መጠቀም፤

፮/ በቡና ማሳው ላይ በባለሙያ ያልተመሰከረለትና ጥቅም ላይ እንዲውል ያልተፈቀደ ኬሚካል መጠቀም፤

፯/ በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደ በስተቀር ከውጭ እንዲገባ የተፈቀደውን ቡና በማንኛውም መልኩ ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ማዋል እና በጥሬው መልክ መልሶ ወደ ወጪ መላክ፤

13/ Export coffee, after fulfilling the necessary procedures and dispatch, shall be monitored and inspected that it exits through legal exit points of the country.

38. <u>Prohibitions</u>

Without prejudice to the prohibitions provided in the proclamation, for any coffee producer or processor, in the course of collecting, processing or storing or transporting supplying coffee, it is prohibited to:

1/ Pick immature coffee or mix red cherry with green or different coffee;

2/ Jumble coffee with soil or mix coffee with alien substances or Place coffee into water with intent to increase its weight;

3/ Scatter coffee on road for pulping; Crashing coffee on asphalt road or processing coffee with backward traditional method and adulterating with unknown elements;

4/ collect green leaves by force and supply it to the market;

5/ Use coffee sacks or equipment other than those approved by the Authority or the appropriate regional organ;

6/ Use chemicals not verified or recommended by professional on his coffee farm;

7/ Use Imported raw coffee for domestic consumption and re-export in raw form unless permitted in special circumstance;

https://chilot.me



፰/ ቡና አምራች አርሶ አደር ቡናን ወደ መጀመሪያ ደረጃ ቡና ግብይት ማዕከል ሲያጓጉዝ ካልሆነ በስተቀር ባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል ሳይፈቅድ የቡና ምርትን በማንኛውም ተሽከርካሪ፣ ጋሪ እና በጋማ ከብት ከቦታ ቦታ ማዘዋወር፤

፱/ ከባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ካለው የክልል አካል ፈቃድ ውጪ የወጪ ቡና በማንኛውም መደብር ወይም ቦታ ማከማቸት ወይም መገበያየት፤

፲/ ለውጪ ገበያ የተዘጋጀ ቡና ለመሸጥ በሚፈቀዱ ቦታዎች ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የተዘጋጀ ቡና መሸጥ፤ እና

፲፩/ አግባብ ካለው የክልል አካል ህጋዊ ፈቃድ ሳይሰጠው በመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከል ገብቶ መገበያየት፤

የተከለከለ ነው፡፡

## ፴፱. <u>የቡና ጥራትና ግብይት ተቆጣጣሪዎችን ስለመመደብ</u>

፩/ እንደአግባብነቱ ባለሥልጣኑና አግባብ ያለው የክልል አካል የቡና የጥራት ተቆጣጣሪ እና የቡና ግብይት ተቆጣጣሪ ይመድባሉ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ መሠረት የሚመደብ የቡና ጥራት እና የቡና ግብይት ተቆጣጣሪ በቂ ዕውቀት፣ ክህሎት እና መልካም ስነ ምግባር ያለው መሆን አለበት፡፡

## ፵. <u>የቡና ጥራት ተቆጣጣሪ ሥልጣንና ተግባር</u>

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፱ መሠረት የተመደበ የቡና ጥራት ተቆጣጣሪ ስለቡና ጥራት ቁጥጥር የተደነገጉ ድንጋጌዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ የሚከተለው ስልጣን ይኖረዋል:-

ሀ) በመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት እና በቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች የሚቀርበውን ቡና ጥራት ሁኔታ መከታተል፣ መቆጣጠር፤

8/ Transport any coffee by any vehicle, cart or animal without permission of Authority and appropriate regional organ except for coffee growing farmers when transporting to first level transaction center;

9/ Store or transact export coffee at any place without permission of the Authority or appropriate regional organ;

10/ Sell domestic consumption coffee at permitted places to sell export coffee; and

11/ Transact at first level coffee transaction centers without license obtained from appropriate regional organ.

## 39. <u>Assignment of Coffee Quality and Transaction Inspectors</u>

1/ The Authority and the appropriate regional organs shall, as may be appropriate, assign coffee quality and transaction inspectors.

2/ A person to be assigned as inspector pursuant to sub-article (1) of this Article shall have adequate knowledge and skill with good ethical background.

## 40. <u>Powers and Duties of Coffee Quality Inspector</u>

1/ A coffee quality inspector assigned pursuant to Article 39 of this Regulation, shall have the following powers and duties to inspect and control:

a) coffee quality delivered to processing industries and primary coffee transaction centers;

https://chilot.me



ለ/ አነስተኛ ይዞታ ባላቸው ቡና አምራች አርሶ አደሮችና ቡና አልሚ ባለሃብቶች የሚካሄደውን የቡና አዘገጃጀት፣ አከመቻቸት እና የማጓጓዝ ሂደት መከታተል መቆጣጠር፤

ሐ/ በቡና አቅራቢዎች፣ በቡና ላኪዎች፣ በኅብረት ሥራ ማህበራት፣ በቡና ቆዪዎች እና በቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪዎች የሚከናወነ ውን የቡና ክምችትና ዝግጅት መከታተል፣ መቆጣጠር፤ እና

መ) ከውጭ በግገር የሚገባውን የጥሬ ቡና ጥራትና ዝግጅት ሂደት መቆጣጠር፡፡

፪/ የቡና ጥራት ተቆጣጣሪ የጥራት ቁጥጥርን በሚመለከት ለሚመለከተው አካል ወቅታዊ ሪፖርት ማቅረብ፡፡

## ፵፩. <u>የቡና ግብይት ተቆጣጣሪ ሥልጣንና ተግባራት</u>

፩/ የቡና ግብይት ተቆጣጣሪ በአዋጁ፣ በዚህ ደንብ እና ለወደፊት በሚወጣ መመሪያ ስለቡና ግብይት ቁጥጥር የተደነገጉ ድንጋጌዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

ሀ) ወደ ማንኛውም የቡና ማዘጋጃና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ወይም የአገልግሎት ሰጪ መሥሪያ ቦታ በሥራ ሰዓት የመግባት፣ ወካይ የቡና ናሙና የመውሰድ፣ የማጣራት፣ ሰነዶችን የመመልከትና ኮፒ የመውሰድ፣ ፎቶ ግራፍ የማንሳት፣

ለ) ከቡና አቅራቢ ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም ወደ ወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ የሚጓጓዝ ቡና ሲጫን በጥራት፣ በእርጥበት መጠኑ እና በቡና ዓይነቱ መዘጋጀቱን የማጣራት፣

ሐ) በቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪዎች እና በመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት የሚቀርበውን ቡና ግብይት የመቆጣጠር፣

b) the activities of harvesting, processing, storing and transporting performed by small scale coffee farmers and commercial coffee farm investors,

c) coffee processing and storing activities by coffee suppliers, exporters, cooperatives, coffee roasters at coffee processing and storage industries and

d) the quality and preparation process of imported coffee from abroad.

2/ Coffee quality inspector shall provide timely report on quality inspection to relevant organ.

## 41. <u>Powers and Duties of Coffee Transaction Inspector</u>

1/ To assure the proper implementation of the coffee quality control provisions of the proclamation, this regulation and directives to be issued, a coffee transaction inspector shall have the following powers and duties:

a) Inspect any processing and warehouse industry or service provider site during working hours and can take a representative sample, inspect, look on and take a copy of documents, take a photo,

b) Check delivery and transportation of coffee from supplier to Ethiopia Commodity Exchange or Export Processing Industry with recommended quality, moisture content and coffee type,

c) Control coffee transaction at coffee processing industries and primary coffee transaction centers,

https://chilot.me



መ) የአቅርቦትና የወጪ ቡና ክምችት መጠን፣ አያያዝ፣ አስተሻሸግና ማጓጓዝ ሂደት የመከታተልና መቆጣጠር፣

ሠ) አስፈላጊ በሆነበት ጊዜና ወቅት በቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪዎች ተገኝቶ የቡና ክምችት ቆጠራ የማካሄድ፣

ረ) የወጪ ቡና ሽያጭ በውሉ መሠረት መፈጸሙን የመቆጣጠር እና በውሉ መሠረት በአልተፈጸመ ጊዜ አጣርቶ እርምጃ እንዲወሰድ የማድረግ፣

ሰ) በልማትና ግብይት ትስስር የሚፈጸመውን የቡና ግብይት ሂደትና አፈጻጸም የመከታተልና የመቆጣጠር፣

ሸ) የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ጅምላና ችርቻሮ ንግድን የመቆጣጠር፣

ቀ) በየደረጃው የሚጓጓዝ የአቅርቦት፣ የሀገር ውስጥ ፍጆታና የወጪ ንግድ ቡና አጣርቶ በፐሎምፐ በማሸግ የመሸኘት፣

በ/ ቡና የሚያጓጉዝ ተሽከርካሪ በማስቆም መፈተሽና አግባብነት ያላቸው ሠነዶች እንዲቀርቡለት የመጠየቅ፣ እና

ተ) በኬላ ላይ የህገወጥ ቡና ንግድና ዝውውር ቁጥጥር የማካሄድ፣

፪/ የቡና ግብይት ተቆጣጣሪ ህጉን በመጣስ ህገወጥ የቡና ግብይት ድርጊት ተፈጽሟል ብሎ በበቂ ሁኔታ ሲጠረጠር አግባብነት ባለው ህግ መሠረት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም አስቸኳይ ሁኔታ ሲኖር ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ከፍትህ አካላት ወይም ከፀጥታ አካላት ጋር በመተባበር ደረሰኝ ሰጥቶ ቡናውን ይይዛል ወይም የቡናውን ናሙና ወስዶ ቡናው የተከማቸበትን ቦታ ያሽጋል፡፡

d) inspect and control Coffee stock quantity, handling, packaging and transportation process,

e) Take coffee stock inventory at any time when necessary in coffee processing and warehouse industries,

f) inspect and control Performance of export coffee contract and Investigate defaults and propose measures to be taken,

g) inspect and control Coffee transactions and performance of out grower's scheme,

h) control Coffee wholesalers and retailers Domestic consumption coffee, performance of export coffee sales contract;

i) inspect Packing and Sealing of supply coffee, domestic consumption coffee and export coffee transported at any level;

j) Stop any vehicle transporting coffee and demand the presentation of pertinent documents, and

k) Control Illegal coffee trade and movement at check points,

2/ Where a coffee transaction inspector suspects with sufficient ground that un illegal act committed, may seize the coffee with court warrant or without court warrant in forcing circumstances in accordance with criminal procedure law, in collaboration with relevant justice and security organs, against issuance of receipt or take a sample of the coffee and seal the warehouse where the coffee is deposited.

https://chilot.me



፫/ የቡና ግብይት ተቆጣጣሪ ከጠቅላላ የመጫን ክብደቱ መጠን ግማሽና ከዚያ በላይ ቡና በመጫን ተሽከርካሪው ህገ ወጥ ተግባር መፈፀሙን በበቂ ምክንያት ሲያምን እና አግባብነት ባለው የወንጀል ሥነ ሥርዓት ህግ መሠረት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም አስቸኳይ ሁኔታ ሲኖር ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ከፍትህ አካላት ወይም ከፀጥታ አካላት ጋር በመተባበር የመረከቢያ ደረሰኝ በመስጠት ተሽከርካሪውን ይይዛል፤

፬/ የቡና ግብይት ተቆጣጣሪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) መሠረት ስለወሰደው እርምጃ ወዲያውኑ ለባለስልጣኑ ወይም አግባብ ላለው የክልል አካል ሪፖርት ያድርጋል፤ በዚህ ደንብ መሠረት መወሰድ ስላለባቸው ተከታይ እርምጃዎች ከባለስልጣኑ ወይም አግባብነት ካለው የክልሉ አካል የሚሰጠውን መመሪያ ይፈጽማል፡፡

፭/ የቡና ግብይት ተቆጣጣሪ የቡና ግብይት ቁጥጥርን በሚመለከት ለሚመለከተው አካል ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

**፵፪. ህገወጥ ድርጊቶችን ስለመጠቆም**

፩/ ማንኛውም ሰው በቡና አዘገጃጀት፣ ክምችት፣ ማጓጓዝ ወይም ግብይት ሂደት ህገወጥ ድርጊት መፈጸሙን ሲያውቅ በአካባቢው ለሚገኝ የቡና ግብይት ተቆጣጣሪ ወይም ለባለስልጣኑ ወይም አግባብነት ላለው የክልል አካል ወይም የጸጥታ አካላት በአካል፣ በጽሁፍ፣ በኤሌክትሮኒክስ መልዕክት መጠቆም ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ጥቆማ አቅርቦ ሕገወጥ ድርጊት የተፈጸመበትን ቡና ያስያዘ እና የያዘ ማንኛውም ሰው በዚህ ደንብ አንቀጽ ፵፫ (፲፩) (ለ) መሠረት የጠቋሚ ወይም የያዥ አበል ይከፈለዋል፡፡

3/ Where coffee transaction inspector suspects, illegal act committed by a vehicle loaded with coffee half and above of its total loading capacity, shall seize the vehicle, against issuance of receipt, with court warrant or without court warrant in forcing circumstance in accordance with criminal procedure law, in collaboration with relevant justice and security organs.

4/ The coffee transaction inspector shall immediately report to the Authority or appropriate regional organ about the action taken pursuant to sub-article (2) and (3) of this Article and follow the instructions of the Authority or appropriate regional organ for taking subsequent actions.

5/ Coffee transaction inspector shall provide timely report on coffee transaction inspection to relevant organ.

**42. Whistle blowing Illegal Acts**

1/ Any person, who is aware of an illegal act committed in the course of processing, storing or transporting, or transaction may inform in physical presence, in writing, with an electronic message to the nearest coffee quality and transaction inspector or regional security organs, to the Authority or the appropriate regional organ.

2/ Any person who has submitted a report in accordance with sub-article (1) of this Article, that led to the seizure of coffee subject to the illegal act, shall be entitled to the payment of whistle blower's commission pursuant to article 43 (11) (b) of this Regulation.

https://chilot.me



**፵፫. ስለተያዘ ቡና**

፩/ በበቂ ጥርጣሬ ህገወጥ ነው ተብሎ የተያዘ ቡና ተጣርቶ ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ:-

ሀ) ቀይ እሸት ቡና ከሆነ በ፰ ሰዓት ውስጥ በአቅራቢያው ወደሚገኝ የመጀመሪያ ደረጃ የቡና ግብይት ማዕከል ቀርቦ በዕለቱ መሸጫ ዋጋ ተሸጦ በወረዳው በሚገኝ አግባብ ባለው የክልል አካል ለዚሁ ተብሎ በተከፈተ ዝግ የባንክ ሒሳብ መቀመጥ አለበት፡፡

ለ) ጀንፈል ቡና ከሆነ በወረዳው ወይም በከተማ አስተዳደሩ በሚገኝ አግባብ ባለው የክልል አካል በተዘጋጀ መጋዘን መጠኑ ታውቆ መቀመጥ አለበት፡፡

ሐ) የአቅርቦት ወይም የወጪ ገበያ ቡና ከሆነ በ፵፰ ሰዓት ውስጥ በአቅራቢያው ወደሚገኝ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ መጋዘን መጠንና ደረጃው ተለይቶ በህጋዊ ደረሠኝ ገቢ ሆኖ መቀመጥ አለበት፡፡

መ) ለቡናው ባለቤት ወይም ተወካይ የተያዘው ቡና ዓይነትና መጠን ተገልጾ እንደዚሁም የአቅርቦት ወይም የወጪ ገበያ ቡና ከሆነ የቡናው ደረጃም ጭምር ተገልጾ ህጋዊ ደረሰኝ መሰጠት አለበት፡፡

፪/ በህገ ወጥ መንገድ ቡና በመጫን ወይም በማጓጓዝ በበቂ ሁኔታ ተጠርጥሮ የተያዘ ተሽከርካሪ ተጣርቶ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ በአቅራቢያው በሚገኝ የሚመለከተው የፖሊስ አካል ተይዞ መቆየት አለበት፡፡

፫/ ማንኛውም አሽከርካሪ እንዲጭን ከተፈቀደለት ቡና ውጪ በየትኛውም የተሽከርካሪው አካል ላይ ተጨማሪ ቡና ወይም ቡና ያልሆነ ሌላ ጭነት ወይም ምርት አዳብሎ ጭኖ የተያዘ እንደሆነ በተጨማሪነት ለተጫነው ቡና ምርት እንደአግባብነቱ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩)(ለ)እና(ሐ) በተደነገገው መሰረት ይፈጸማል፡፡

**43. Seized Coffee**

**1/** Coffee seized with reasonable suspicion of illegality, until decisions made, shall be:

a) Supplied to nearest first level coffee transaction center within 8 hours and sold with existing sell price and shall be saved in closed bank account opened by appropriate regional organ of the Woreda, if it is red cherry coffee.

b) Stored with its amount specified in by appropriate regional organ of Woreda or city administration in the prepared warehouse, if it is coffee with pulp.

c) Stored with legal receipt identifying its quantity and quality at nearest Ethiopian Commodity Exchange warehouse within 48 hours, if it is supply or export coffee.

d) Provided with legal receipt for the owner or representative by identifying seized coffee type, quantity and in addition its grade when it is supply or export coffee.

2/ Any vehicle, loading and transporting coffee, seized with reasonable suspicion of illegality, shall be stayed at relevant nearby police station, until investigation and decision is made.

3/ When any driver seized loading extra coffee or any other load or product on any parts of the vehicle beyond permitted coffee load, the extra load shall be stored by identifying its quantity and type in accordance with sub article (1) (b) and (c) of this Article as may appropriately so.

https://chilot.me



፬/ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ በተደነገገው መሠረት ህገ ወጥ ተግባር የተፈጸመበት ቡና ወይም ተሽከርካሪ የያዘ ሰው ለባለስልጣኑ ወይም አግባብ ላለው የክልል አካል ለውሳኔ አስፈላጊ የሆነ መረጃና ማስረጃ አያይዞ በ፵፰ ሰዓት ውስጥ ማቅረብ አለበት፡፡

፭/ በዚህ ደንብ መሠረት ስለተያዘ ቡና፣ ተሽከርካሪ፣ ተጨማሪ ጭነት ወይም ምርት በሚመለከት ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ቅሬታውን በማስረጃ አስደግፎ በሚከተለው አግባብ ሊያቀርብ ይችላል:-

ሀ) ቀይ እሸት ወይም ጀንፈል ቡና ወይም ከዚህ ጋር የተያያዘ ተሽከርካሪ፣ ተጨማሪ ጭነት ወይም ምርት ሲሆን ደረሰኝ ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ በሦስት የሥራ ቀናት ውስጥ በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር ደረጃ ላለ ባለስልጣን ወይም አግባብ ላለው የክልል አካል ሊያቀርብ ይችላል፣

ለ) የአቅርቦት ወይም የወጪ ገበያ ቡና ወይም ከዚህ ጋር የተያያዘ ተሽከርካሪ፣ ተጨማሪ ጭነት ወይም ምርት ሲሆን ደረሰኝ ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለዞን ወይም በዞን ደረጃ ለሚገኝ የከተማ አስተዳደር ባለስልጣን ወይም አግባብ ላለው የክልል አካል ቅሬታውን ሊያቀርብ ይችላል፣

፮/ የተያዘ ቡናን፣ ተሽከርካሪን፣ ተጨማሪ ጭነትን ወይም ምርትን አስመልክቶ የሚሰጥ ውሳኔ በባለስልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል የበላይ ኃላፊ በሚመራ ኮሚቴ ይሆናል፡፡

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭)(ሀ) እና (ለ) መሠረት ቅሬታ የቀረበለት አካል የቀረቡለትን መረጃዎችና ማስረጃዎች መርምሮ:-

4/ Any person, who seizes coffee, vehicle, extra load and other product, shall provide the necessary information and evidence within 48 hours to the Authority or appropriate regional organ.

5/ Any person, who has objection, about seized coffee, vehicle, extra load or product pursuant to this Regulation, may:

a) Submits his objection with evidence, within three working days starting from the date received the receipt, to the Authority or the appropriate regional organ of the Woreda and city administration level, when it is red cherry coffee or coffee with pulp or vehicle or additional load or product related with this,

b) Submit his objection with evidence, within five working days starting from the date received the receipt, to the Authority or the appropriate regional organ of the Zone and city administration at the level of zone, when it is supply or export coffee or vehicle or additional load or product related with this,

6/ Any decision about seized coffee, vehicle, extra load shall be made by a committee led by a high level official of the Authority or the appropriate regional organ of any level.

7/ The organ, who received complaint as per sub-Article (5) (a) and (b ) of this Article, after examining the information and evidence provided, shall:

https://chilot.me



ሀ) ቀይ እሸት ወይም ጀንፈል ቡና ወይም ከዚህ ጋር የተያያዘ ተሽከርካሪ፣ ተጨማሪ ጭነት ወይም ምርት ሲሆን የቅሬታ ማቅረቢያው ቀን በተጠናቀቀ በሁለት የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠትና ወዲያውኑ ለተያዘበት ሰው በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፣

ለ) የአቅርቦት ወይም የወጪ ገበያ ቡና ወይም ከዚህ ጋር የተያያዘ ተሽከርካሪ፣ ተጨማሪ ጭነት ወይም ምርት ሲሆን የቅሬታ ማቅረቢያው ቀን በተጠናቀቀ ሦስት የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠትና ወዲያውኑ ለተያዘበት ሰው በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፣

ሐ) የውሳኔውን ግልባጭ ከነማስረጃው ለባለስልጣኑ ወይም አግባብ ላለው የክልል አካል በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ማድረስ አለበት፡፡

፰/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፯) በተሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ሰው:-

ሀ) ቀይ እሸት ወይም ጀንፈል ቡና ወይም ከዚህ ጋር የተያያዘ ተሽከርካሪ፣ ተጨማሪ ጭነት ወይም ምርት ከሆነ በዞን ደረጃ ላለው አግባብ ያለው የክልል አካል፣

ለ) የአቅርቦት ቡና ሆኖ ቅሬታ አቅራቢው ቡና አቅራቢ ከሆነ አግባብ ላለው የክልል አካል፣

ሐ) የአቅርቦት ወይም የወጪ ገበያ ቡና ሆኖ ቅሬታ አቅራቢው ቡና ላኪ ከሆነ ለባለስልጣኑ፤

በአምስት የሥራ ቀናት ቅሬታውን ማቅረብ አለበት፡፡

፱/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፰) መሠረት ቅሬታ የቀረበለት ባለሥልጣን ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል አቤቱታውን በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ መርምሮ:-

a) Deliver decision and immediately notify the applicant in written form within two working days after the expiry of the complaint date, when it is a red cherry coffee or coffee with pulp or related vehicle, or extra load or product,

b) Deliver decision and immediately notify the applicant, in written form, within three working days after the expiry of the complaint date, when it is supply or export coffee or related vehicle, or extra load or product,

c) Submit a copy of the decision, with complete evidence, to the Authority or appropriate regional organ within five working days.

8/ A person, who has compliant against the decision taken under sub-Article (7) of this Article, may submit within five working days, to:

a) The Appropriate regional organ of the Zone level, if it is red cherry coffee or coffee with pulp or related vehicle, or extra load or product,

b) The Appropriate regional organ, if it is supply coffee and the compliant is coffee supplier,

c) The Authority, if it is supply or export coffee and the compliant is coffee exporter.

9/ The Authority or the relevant regional organ, who receives the complaint in accordance with sub-article (8) of this Article, after examining the application, within five working days:

https://chilot.me



ሀ) የተሰጠውን ውሳኔ የሚሽር ከሆነ ወዲያው የተያዘውን ቡና፣ ተሽከርካሪ፣ ተጨማሪ ጭነት ወይም ምርት ወይም የተሸጠበትን ገንዘብ ለአመልካቹ እንዲመለስ ማድረግ አለበት፣

ለ) የተሰጠውን ውሳኔ ካጸናው ወይም ቅሬታ በጊዜ ገደቡ ያልቀረበ እንደሆነ የተሰጠውን ውሳኔ አጽንቶ ለቅሬታ አቅራቢው በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፤

ሐ) በዚህ ንኡስ አንቀጽ (ለ) መሠረት ውሳኔውን ያጸናው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፲) መሠረት በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ለፍርድ ቤቱ አቤቱታ ያልቀረበ ከሆነ የተያዘው ቡና በኢትዮጵያ ምርት ገበያ፤ ተሽከርካሪው ወይም ተጨማሪ ጭነቱ ወይም ምርቱ በግልጽ ጨረታ ተሽጦ ከእነዚህ የሚገኝ ገንዘብ በዝግ የባንክ ሂሳብ እንዲቀመጥ ማድረግ አለበት፡፡

፲/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱)(ለ) የተመለከተውን ውሳኔ የሚቃወም የቡና፣ የተሽከርካሪ፣ የተጨማሪ ጭነት ወይም የምርት ባለቤት ውሳኔው በደረሰው በ፴ (ሰላሳ) የሥራ ቀናት ውስጥ ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ አለበት፡፡

፲፩/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፲) መሠረት አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት እንደአግባቡ የባለስልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል የሰጠውን ውሳኔ:-

ሀ) የሻረው እንደሆነ ቡናውን፣ ተሽከርካሪውን፣ ተጨማሪ ጭነቱን ወይም ምርቱን ወይም የሸያጩን ገንዘብ ለማጓጓዣና ከሽያጭ ጋር የተያያዙ ወጪዎች እንዲቀነሱ ተደርጎ ለባለቤቱ እንዲመለስ ይደረጋል፤

a) Shall immediately return the seized coffee, vehicle, extra load or product or proceedings of sale to the applicant, if it decided to reverse the decision given;

b) Shall uphold the decision and notify the complaint after delivery of the decision, if it sustains the decision given or compliant is not submitted within the time limit;

c) Shall deposit, in a closed bank account, the money obtained from sale of coffee at Ethiopian commodity exchange or sale of vehicle or extra load or product at open auction, if no appeal is submitted to the court, within the specified time limit provided under sub article (10) of this article, about coffee or vehicle, extra load or product which its illegality affirmed by the decision pursuant to paragraph (b) of this sub article.

10/ The Coffee, vehicle, extra load or product owner, who objects the decision given under Sub-Article 9 (b) of this Article, may appeal to the relevant court, within 60 (sixty) working days of the decision.

11/ Where the Court to which an application is submitted pursuant to sub-article (10) of this Article as appropriate if :

a) Reverses the decision of the Authority or the relevant regional organ, the proceeds of the coffee, the vehicle, the extra load or the product sale shall be, after deducting expenses related to transportation and transaction, returned to the owner;

https://chilot.me



ለ) ያጸናው ወይም ባለቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፲) በተቀመጠ የጊዜ ገደብ ውስጥ አቤቱታ ያላቀረበ እንደሆነ ባለስልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል ከማጓጓዝና ከሽያጭ ጋር የተያያዙ ወጪዎችን ተቀናሽ አድርጎ የሽያጭ ገንዘቡ ለማበረታቻነት ፳ በመቶ (ሃያ በመቶ) ለጠቋሚ፣ ፳ በመቶ (ሃያ በመቶ) ለያዥ እና ፳ በመቶ (ሃያ በመቶ) ለባለስልጣኑ ወይም አግባብ ላለው የክልል አካል ለሎጂስቲክስና ለቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ፣ ፳ በመቶ (ሃያ በመቶ) ለህገወጥ ቡና በመቆጣጠር በቀጥታ ለሚሳተፉ ተቋማት አቅም ግንባታ እና ቀሪው ፳ በመቶ (ሃያ በመቶ) ቡናው በተያዘበት አስተዳደር እርከን ለአካባቢ ልማት እንዲውል ያደረጋል፤

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ለ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጠቋሚ በሌለበት ሲሆን የሽያጭ ገንዘቡ ፴ በመቶ (ሰላሳ በመቶ) ለያዥ፣ ፴ በመቶ (ሰላሳ በመቶ) ህገወጥ የቡና ንግድና ዝውውር ለመቆጣጠር በቀጥታ ለሚሳተፉ ተቋማት አቅም ግንባታ እንዲውል ይደረጋል፤ አፈጻጸሙ ይህን ደንብ ተከትሎ በሚወጡ መመሪያዎች መሠረት ይሆናል፡፡

## ክፍል ስድስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፵፬. የመተባበር ግዴታ

፩/ ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ በማስፈጸም ረገድ ከባለስልጣኑ ወይም አግባብ ካለው የክልል አካል ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

፪/ የቡና ግብይት ተቆጣጣሪ በዚህ ደንብ መሠረት ህገወጥ ድርጊት የተፈጸመበትን ቡና ለመያዝ በሚያደርገው እንቅስቃሴ በየደረጃው የሚገኙ የጸጥታ አካላት እንዲሁም የሚመለከታቸው የመስተዳድር አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

b) Upholds the decision or the owner fails to submit application within the specified time limit under sub-Article (10) of this Article, the Authority or appropriate regional organ shall, after deducting the expenses related with transportation and transaction pays, out of the proceeds of the sale, 20% twenty percent) for whistle blowers, 20% (twenty percent) for Seizure, 20% (twenty percent) for the Authority's or regional organ's logistics and technological capacity building, 20% (twenty percent) for capacity building of seizure organ, who directly participate in illegal coffee regulation and remaining 20% (twenty percent) for local development of administrative level, where the coffee is seized;

c) Without prejudice to the provisions of this sub-article (b) the proceeds of the sale shall be used, 30% ( thirty Percent) for seizure and 30% (thirty Percent) for capacity building of seizure organ who directly participate in illegal coffee regulation, when there is no whistle blower; the execution will be based on directive issued following this Regulation.

## SECTION SIX
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 44. Duty to Cooperate

1/ Any person shall have the duty to cooperate with the Authority or the appropriate regional organ in the implementation of this Regulation.

2/ Security organs of any level or administrative organ shall provide the necessary assistance to a coffee transaction inspector, in seizing, coffee subjected to illegal acts.

https://chilot.me



**፵፭. የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ህጎች**

፩/ የቡና ጥራት ቁጥጥርና ግብይት ደንብ ቁጥር ፩፻፷፩/፪ሺ፩ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

፪/ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ ደንብ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**፵፮. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

ማንኛውም በቡና ንግድ ወይም በአገልግሎት ሰጪነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ያለው ሰው ይህ ደንብ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ስድስት ወራት ከባለስልጣኑ ወይም አግባብ ካለው የክልል አካል በዚህ ደንብ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት ያለበት ሲሆን ይህን እስኪያገኝ ድረስ ባለው የጸና የንግድ ፍቃድ ሥራውን ማካሄድ ይችላል፡፡

**፵፯. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጥቅምት ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

ዶ/ር አብይ አህመድ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

**45. Repealed and inapplicable laws**

1/ Coffee quality control and marketing regulation number 161/2009 is hereby repealed.

2/ Any rule, directive or customary practice that is inconsistent with the provisions of these Regulations shall not apply to the matters covered by this Regulation.

**46. Transitory provisions**

Any person, who has certificate of competence of coffee trading or service providing, shall have to obtain certificate of competence as per this regulation from the Authority or the appropriate regional organ within six months after the issuance of these Regulations, until he obtains a certificate of competence, he may continue operating his business using his existing valid trade license.

**47. Effective Date**

This Regulation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 2nd day of November 2018.**

**ABIY AHMED (DR.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**